የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና ማኅበረሰብ አገልግሎት መመሪያ

# Directive on Research, Technology Transfer, University-Industry Linkage and Community Services for Higher Education Institutions

**መመሪያ ቁጥር: ምርምር 01/2011**
ነሐሴ 2011 ዓ.ም

**Directive No: Research 01/2019**
August 2019

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር**

**Federal Democratic Republic of Ethiopia**

**Ministry of Science and Higher Education**

## አንቀጽ

ክፍል አንድ:- ጠቅላላ ድንጋጌዎች ……………………1-5

ክፍል ሁለት:- ምርምር ……………………………… 6-21

ክፍል ሦስት:- የቴክኖሎጂ ሽግግርና የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር

ንዑስ ክፍል 1:- የቴክኖሎጂ ሽግግር………. 22- 39

ንዑስ ክፍል 2:- የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር …………………………… 40- 42

ክፍል አራት:- የማኅበረሰብ አገልግሎት ………. 43- 46

ክፍል አምስት: አስተዳደር፣ ሥነምግባር፣ ደረጃዎች፣ መርሆዎችና ግብዓቶች

ንዑስ ክፍል 1:- አስተዳደር ………………… 47- 53

ንዑስ ክፍል 2:- ሥነምግባር፣ ደረጃዎችና መርሆዎች ………………………… 54- 66

ንዑስ ክፍል 3:- ግብዓቶች …………………… 67- 74

ክፍል ስድስት:- ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ……….. 75- 79

## Articles

Part One: General Provisions ……………1-5

Part Two: Research …………………… 6-21

Part Three: Technology Transfer and University- Industry Linkage

Section 1: Technology Transfer …. 22-39

Section 2: University- Industry Linkage ……………………. 40-42

Part Four: Community Service ………… 43- 46

Part Five: Governance, Ethics, Standards, Principles and Resources

Section 1: Governance ………….. 47- 53

Section 2: Ethics, Standards and Principles………………….54- 66

Section 3: Resources ……………. 67- 74

Part Six: Miscellaneous Provisions ……75- 79

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና ማኅበረሰብ አገልግሎት መመሪያ

## መግቢያ

ለአገሪቱ ዘላቂና ሁለገብ ልማት መረጋገጥ አስተዋጽዖ ማድረግ ይቻል ዘንድ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የዳበረ የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ሥርዓትን መዘርጋትና ማስተባበር እንደሚያስፈልግ መንግሥት በጽኑ ያመነ በመሆኑ፤

የተበታተነውንና ያልተደራጀውን የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ሥርዓት፣ በአገር ደረጃ የተዋደደና ቅንጅት ያለው እንዲሆን በማድረግ፣ ውጤታማ የሆነ እንዲሁም በሁሉም እርከን ተዓማኒነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራር እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ፤

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በኢንዱስትሪ መካከል አጋርነትና ትብብርን በማሳደግ፣ አቅማቸውን የሚገነባና የኢንዱስትሪዎችን መሠረታዊ ችግሮች የሚፈታ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑና፣ ይህም የማኅበራዊ ችግር ፈች ምርምሮችን በማዳበር አገራዊ ልማትን የሚያሳድግ መሆኑን በመገንዘብ፣

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአጋርነትና በትብብር ከተለያዩ ኢንዱስትሪዎችና ተቋማት የሚያገኙትን የገንዘብ ድጋፍና ገቢ በአግባቡና ወጪን ውጤታማ በሚያደርግ አሠራር ለማስተዳደር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣ እንዲሁም

የተደራጀ የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራትን በእያንዳንዱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በውጤታማነት ለመተግበር አጠቃላይ የአመራር ስርዓት መሰረታዊ በመሆኑ፤

# Directive on Research, Technology Transfer, University-Industry Linkage and Community Services for Higher Education Institutions

## Preamble

*Whereas*, Government strongly believes that it is mandatory to put in place and coordinate a well-developed system of Research, Technology Transfer (TT), University-Industry Linkage (UIL) and Community Services (CS) in Higher Education Institutions (HEIs) to contribute in ensuring sustainable and holistic development across the nation;

*Whereas*, fragmented and disorganized system of Research, TT, UIL and CS of HEIs should have a harmonized and well integrated system so as to create nationally coordinated and Compatible scheme for effective results and to put trustworthy and accountable system in place at all levels;

*Whereas*, it is essential to put in place a system that develops partnership and collaboration between HEIs and Industries that would enhance their capacity and help to solve basic problems of industries; and recognizing that this enriches research undertakings that address and solve community problems thereby enhancing national development;

*Whereas*, it is important to institute a strong system in the HEIs to manage grants and revenues properly and in a cost effective way, which they get from different industries and institutions through partnership and collaborative work; and

*Whereas*, it is fundamentally important to set an overall governance system in HEIs to run organized Research, TT, UIL and CS activities for effective implementation in their respective institutions;



ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና ማኅበረሰብ አገልግሎት መመሪያ" ተብሎ ይጠቀሳል፡፡

**፪. <u>የፆታ አገላለጽ</u>**

በግልጽ ወይም በቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠ በቀር በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፁ ድንጋጌዎች ለሴት ፆታም ተግባራዊ ናቸው፡፡

**፫. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ:

፩) "**አካዳሚክ ሠራተኛ**" ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በማስተማር፣ በምርምር፣ በማኅበረሰብ አገልግሎት እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባር ላይ የተሠማራ የተቋም ሠራተኛ ሲሆን ሴኔት በሚያወጣው ደንብ መሰረት የአካዳሚክ ሰራተኛ ተብሎ ዕውቅና የተሰጠው ሌላ የተቋሙ ባለሙያን ይጨምራል፡፡

፪) "**የትምህርት ክፍል**" ማለት የአንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም አካል የሆነ ኮሌጅ፣ ፋከልቲ፣ ትምህርት ቤት፣ ኢንስቲትዩት፣ ዲፓርትመንት፣ ማዕከል ወይም ዩኒት ወይም ሌላ መጠሪያ የተሰጠው ዩኒት ነው፡፡

፫) "**ተግባራዊ ምርምር**" ማለት ተለይቶ የተገለፀ የተግባር ግብና ዓላማን በሚመለከት የሚካሄድ ምርምር ሲሆን በዋናነት ተለይተው ለተገለፁ ችግሮች መፍትሔ መሻት ነው፡፡

፬) "**ደራሲ**" ማለት የአዕምሮ ውጤት በጥናታዊ ጽሁፍ፣ በመጽሐፍ ወይም ሌላ ምሁራዊ ሥራ ያመነጨ ሰው ነው፡፡

፭) "**መሠረታዊ ምርምር**" ማለት ጥናት በሚደረግበት መስክ ያለውን የዕውቀትና የመረዳት ደረጃ ለማሳደግ ወይም ምሉዕነት እንዲኖረው ለማስቻል የሚደረግ ምርምር ነው፡፡

፮) "**የተቋማት ክላስተር**" ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስብስብ ሆኖ፣ ከመካከላቸው አንዱ በአቅራቢያው የሚገኙትን እያስተባበረ የተቋማቱን ግብዓቶች በማቀናጀት ከፍተኛውን ጠቀሜታ ለማስገኘት የተመሠረተ ነው፡፡

This Directive is issued by the Ministry of Science and Higher Education of the Federal Democratic Republic of Ethiopia pursuant to the power vested in it by the Ethiopian Higher Education Proclamation No. 1152/2019.

## Part - One
## General Provisions

**1. *Short Title***

This Directive shall be cited as "Directive on Research, Technology Transfer, University-Industry Linkage and Community Service for Higher Education Institutions".

**2. *Gender Reference***

Unless explicitly stated or implied from the context, provisions of this directive set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

**3. *Definition***

In this Directive, unless the context requires otherwise:

1) "**Academic Staff**" means a member of a higher education institution employed in the capacity of teaching, research, community services and technology transfer activities of the institution, and any other professional of the institution who shall be recognized so by senate statutes.
2) "**Academic Unit**" means a college, faculty, school, an institute, a department, a center, or a unit with any other designation established as a constituent unit of a higher education institution.
3) "**Applied Research**" means an investigation which is directed primarily toward specific practical aims or objectives including solving specific problem/s.
4) "**Author**" means a person who has intellectually created a work in an article, a book or any other scholarly work.
5) "**Basic Research**" means an investigation with the primary aim of developing complete knowledge or understanding of the subject under study.
6) "**Cluster Institutes**" means a group of HEIs of which one coordinates the rest in its vicinity in the concept of resource clubbing for optimum utilization.

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

፯) “**የትብብር ምርምር**” ወይም “**የጋራ ምርምር**” ማለት ለምርምር በተደረገ የትብብር ስምምነት መሠረት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም፣ ኢንዱስትሪ፣ ወይም ሌላ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም በጋራ የሚያከናወኑት ሣይንሳዊ ጥናት ወይም የምርምርና ልማት ፕሮጀክት ነው፡፡

፰) “**ማኅበረሰብ**” ማለት (ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውጭ ባለው ትርጉም) የከፍተኛ ትምህርት ተቋም አካል ያልሆኑ ሰዎች ወይም ተቋማት ማለት ነው፡፡

፱) “**የጥቅም ግጭት**” ማለት በአንድ ግለሰብ የግል ፍላጎትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ባለ የግለሰቡ ሙያዊ ግዴታ መካከል ያለ ልዩነት ሲሆን የጥቅም ግጭት አለ የሚባለው በገለልተኛ አካል እይታ የግለሰቡ የሙያ ተግባርና ውሳኔ አሰጣጥ በግል ጥቅም፣ በገንዘብ ጥቅም ወይም በሌላ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል አመክንያዊነት ያለው ጥርጣሬ ሊኖር ከቻለ ነው፡፡

፲) “**የማማከር አገልግሎት**” ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም አካዳሚክ ሠራተኛ ለማኅበረሰቡ የሚሰጥ የሙያ ወይም የቴክኒክ አገልግሎት ነው፡፡

፲፩) “**የኮንትራት ምርምር**” ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሙያ ብቃቱንና የመገልገያ መሣሪያውን በመጠቀም ለኢንዱስትሪ ወይም ለሌላ የመንግሥት ወይም የግል ተቋም በግልጽ የተመለከተ ምርምር አካሂዶ፣ በምላሹም ክፍያ የሚያገኝበት ነው፡፡

፲፪) “**የቅጅ መብት**” ማለት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ለባለቤቱ/ቶቹ የሚደረግ ጥበቃ ነው፡፡

፲፫) “**የማኅበረሰብ አገልግሎት**” ማለት ጉዳዩ የሚመለከተው አካል እያወቀ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም አካደሚክ ሠራተኞች ወይም በተማሪዎች አለክፍያ የሚሰጥ ሙያዊ አገልግሎት ሲሆን፣ ዓላማውም የሕዝብ፣ የሕዝብ ተቋሞች ወይም ለትርፍ ላልተቋቋሙ ድርጅቶች መጠቀም ነው፡፡

፲፬) “**ሠራተኛ**” ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሙሉ ወይም የትርፍ ጊዜ ሙያዊ አገልግሎት የሚሰጥና፣ ለዚህም ደመወዝ ወይም ሌላ ክፍያ የሚያገኝ ሰው ነው፡፡

፲፭) “**አስተዳደር (ገቨርናንስ)**” ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ምርምርን፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን፣ ዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርንና የማኅበረሰብ አገልግሎትን በሚመለከት በተቋምና በሚኒስቴር ደረጃ መመሪያዎች፣ ምግባረ ደንቦች፣ ተግባራትና ውሳኔዎች የሚመነጩበት፣ ዘላቂነታቸው የሚረጋገጥበት፣ የሚመሩበት እና ተጠያቂነታቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት ነው፡፡

፲፮) “**የከፍተኛ ትምህርት ተቋም**” ወይም “**ተቋም**” ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁ. 1152/2011 በተገለፀው ትርጉም መሠረት ዩኒቨርሲቲ፣ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ወይም ኮሌጅ ማለት ነው፡፡

7) “**Collaborative Research**” or “**Joint Research**” means a scientific investigation or research and development project undertaken jointly by HEI, industry or other governmental and non-governmental organizations based on a research partnership agreement.

8) “**Community**”(in its usage outside an HEI community) means a group of people/institutions that do not belong to the HEI.

9) “**Conflict-of-Interest**” means divergence between an individual’s private interests and his professional obligations to the HEI such that an independent observer might reasonably question whether the individual’s professional actions or decisions are determined by considerations of personal gain, financial or otherwise.

10) “**Consultancy Service**” means professional or technical service rendered by a staff member of a HEI to the community.

11) “**Contract Research**” means conduct of a specified research project by a HEI for an industry or other public or private organization by using its expertise and equipment in return for the payment of fee.

12) “**Copyright**” means a protection provided by the laws of Ethiopia to its owner/s.

13) “**Community Service**” means any unremunerated professional service that is performed by academic staff or students of HEIs with the knowledge of the responsible office; it is undertaken for the benefit of the public, its institutions, or for non-profit organizations.

14) “**Employee**” means a person who receives a salary or other consideration from the higher education institution for performance of services, part-time or full time.

15) “**Governance**” means the way rules, norms and actions or decisions in relation to research, technology transfer, university-industry linkage and community service at HEIs are produced, sustained, regulated and held accountable both at institution and Ministry levels.

16) “**Higher Education Institution**” or “**Institution**” means a university, university college or college as defined by Higher Education Proclamation No. 1152/2019.

፲፯) "**አገር በቀል ወይም ባህላዊ ዕውቀት**" ማለት ባለቤትነቱ የባህላዊ፣ የአካባቢያዊ፣ ወይም የአገር በቀል ማኅበረሰቦች የሆነ ዕውቀት ወይም ክህሎት ነው፡፡

፲፰) "**ኢንዱስትሪ**" ማለት የግል ወይም የመንግሥት ኩባንያዎች፣ የንግድ ድርጅቶች፣ የመንግሥት ተቋማት እንዲሁም ሌሎች አገልግሎት እና/ወይም ምርት የሚያቀርቡ ድርጅቶች ማለት ነው፡፡

፲፱) "**አዕምሯዊ ንብረት**" ማለት ከፈጠራ፣ ከአሠራር ሂደት፣ ከጥንቅር እንዲሁም ከሌላ አዕምሯዊ ፈጠራ ጋር የተያያዙ መብቶች ስብስብ ነው፡፡ በተለይም፣ የፓተንት፣ የቅጅ መብት፣ የንግድ ምልክት፣ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ መብቶችን እና የንግድ ምስጢርን ያካትታል፡፡

፳) "**የአዕምሯዊ ንብረት መብቶች**" ማለት የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤቶች በአገሪቱ ሕግ መሠረት በሥራቸው ወይም በፈጠራቸው እንዲጠቀሙ የሚያደርጉ መብቶች ናቸው፡፡

፳፩) "**ፈጠራ**" ማለት ጠቃሚ የሆነ ሓሳብ፣ አሠራር፣ ማሺን መፍጠር ወይም የአንድን ቁስአካል ንጥረ-ዉሁድ በማግኘት ትኩረት ለሚሻ የቴክኖሎጂ ችግር መፍትሔ ማግኘት፣ ወይም ለማንኛውም ተግዳሮት አዲስ መፍትሔ መስጠት ነው፡፡

፳፪) "**የፈጠራ ባለቤት**" ማለት አዲስ እና ኦሪጂናል ነገሮች የፈጠረ ወይም የፈጠራ ሥራ ያገኘ ሰው ነው፡፡

፳፫) "**ኢኖቬሽን**" ማለት አሠራርን፣ ምርት/አገልግሎትንና ስትራቴጂን ደረጃ በደረጃ በማሻሻል ወይም በሥርነቀል ሁኔታ በመለወጥ አንድን ነገር በአዲስ መንገድ መከወን ነው፡፡

፳፬) "**የዕውቀት ሽግግር**" ማለት እውቀትን ለመላው ህብረተሰብ ጥቅም ላይ ለሚያውሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ማስተላለፍ ሲሆን ይህም የሚከናወነው በፐብሊኬሽን፣ ተማሪዎችን በማሠልጠንና በማስተማር፣ ምሩቃንን በመቅጠር፣ በኮንፈረንስ፣ በምክክር፣ በትብብር ሥራ፣ እንዲሁም የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ የሚሹና ለንግድ ሥራ አገልግሎት የሚውሉ የፈጠራና የግኝት መብቶችን በመቀበል/በማግኘት ነው፡፡

፳፭) "**የላቦራቶሪ ሠራተኛ**" ማለት መማር-ማስተማርን፣ ምርምርን፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቤተሙከራዎችን፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሂደቶችን፣ የኮምፒዩተር ማዕከላትን፣ ወርክሾፖችንና ማስተማሪያ ሆስፒታሎችን በማገዝ ሥራ ላይ የተመደበ ሠራተኛ ነው፡፡

፳፮) "**ፈቃድ**" ማለት የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤት (ፈቃድ ሰጭ)፣ ያሉትን የአዕምሯዊ ንብረት መብቶች ለሌላ ወገን (ፈቃድ ተቀባይ) በሙሉ

17) "**Indigenous or Traditional Knowledge**" means knowledge or skill owned by cultural, local or indigenous communities or any section of such communities.

18) "**Industry**" means private and public companies, enterprises, government institutions and other organizations that deliver services and/or products.

19) "**Intellectual Property**" means an ensemble of rights related to invention, process, composition, and other creation of the mind. It mainly includes patent, copyright, trademark, industrial design and trade secret.

20) "**Intellectual Property Rights**" are rights that allow owners of intellectual property to benefit from their own work or invention in accordance with the laws of the country.

21) "**Invention**" means a creation of any useful idea, process, machine or discovery of composition of matter which solves a significant technological problem or brings a novel solution to any challenge.

22) "**Inventor**" means a person who has brought new and original elements to an invention.

23) "**Innovation**" means a new way of doing something by improving process, product/ service and strategy either incrementally or radically.

24) "**Knowledge Transfer**" means imparting knowledge to those in the society who can make use of it for the general good through publications, training and education of students, employment of graduates, conferences, consultations, and collaboration as well as by obtaining rights to inventions and discoveries that qualify for intellectual property protection and commercialization.

25) "**Laboratory Staff**" means an academic support staff employed to support the teaching-learning, research and TT processes of HEIs laboratories, computer centers, workshops and teaching hospitals.

26) "**License**" means an agreement-based permission granted by the owner of intellectual property, the licensor, to the other party, the licensee, to use or exploit all or some of the owner's rights.



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

ወይም በከፊል ለመጠቀም እንዲችል የሚሰጥ ስምምነትን መሰረት ያደረገ ፈቃድ ነው፡፡

፳፯) “**የማቴሪያል ዝውውር ስምምነት**” ማለት አንድ ተዋዋይ ወገን፣ ሌላ ወገን ለፍተሻ፣ ለግምገማ፣ ወይም ለሙከራ ይጠቀምበት ዘንድ ቁሳዊ ማቴሪያሎችን ወይም ናሙናዎችን ለመስጠት የሚያደርገው ስምምነት ሲሆን፣ ይህም ከሰው ውጭ የሆኑ ስነ-ህይዎታዊ ማቴሪያሎችን፣ የኬሚካል ውሁዶችን፣ መረጃ ቋት እና ሶፍት ዌር ኮዶችን ይጨምራል፡፡

፳፰) “**ሚኒስቴር**” ወይም “**ሚኒስትር**” በቅደም ተከተል የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር፣ እና ሚኒስትር ማለት ነው፡፡

፳፱) “**አጋርነት**” ሁለት ወይም ከሁለት የበለጡ ወገኖች የጋራ ፍላጎታቸው የሆነን ተግባር በትብብር ለመምራትና ለማከናወን የሚመሠርቱት የግንኙነት ሥርዓት ነው፡፡

፴) “**ፓተንት**” ማለት የፈጠራ ሥራን ለማስጠበቅ ከምርት ወይም ከምርት ሂደት ጋር የተያያዘና ለአዕምሯዊ ንብረት መብት ባለቤት በኢትዮጵያ የአዕምሯዊ ንብረት ህግ መሰረት የተረጋገጡትን የሚያጎናጽፍ መብት ነው፡፡

፴፩) “**ሰው**” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ ሰውነት የተሰጠው ነው፡፡

፴፪) “**የአዕምሮ ሥራ ስርቆሽ**” ማለት የሌላን ሰው የአዕምሮ እና/ወይም አካዳሚያዊ አስተዋጽዖ የራስ አድርጎ ማቅረብና ማስመሰል ነው፣ ይህም፣

(ሀ) ከሌላ ሰው ጽሁፍ ላይ ምንጭ ሳይጠቅሱ መጠቀምን፣

(ለ) ምንጭ ሳይጠቅሱ የሌላን ሰው ጽሁፍ ቃላት ለውጦ ማቅረብን፣

(ሐ) ከተገለፀ ወይም ካልተገለፀ ምንጭ፣ አለጥቅስ ምልክትና የጥቅሱን ገጽ ቁጥር ሳያመለክቱ አራት ወይም ከዚያ የበለጡ ቃላትን በዚያው ቅርፅና ቅደም ተከተል መጠቀምን ያካትታል፡፡

፴፫) “**ዋና ተመራማሪ**” ማለት የገንዘብ ድጋፍ የተደረገለትን ምርምር ወይም ፕሮግራም እንዲመራ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ወይም በገንዘብ ድጋፍ ሰጭ ድርጅት የተመደበ ሰው ነው፡፡

፴፬) “**ምርምር**” ማለት በሥርዓት እየተመራ፣ አዲሰ ጽንሰ ሓሳቦችን፣ ዘዴዎችንና ግንዛቤዎችን ለማመንጨት፣ እንዲሁም አዲስ ወይም የሚታይ ችግርን ለመፍታት አዲስ ዕውቀት ወይም ቴክኖሎጂ መሻት፣ እና/ወይም በወቅቱ የሚገኝን ዕውቀትና ቴክኖሎጂ በአዲስና ፈጠራ በተመላበት መንገድ መጠቀም ነው፡፡

፴፭) “**የምርምርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ካውንስል**”

27) “**Material Transfer Agreement**” means an agreement in which one party agrees to provide physical materials or samples, including non-human biological materials, chemical compounds, databases and software codes, to another party for testing, evaluation, or experimentation.

28) “**Ministry**” and “**Minister**” means, respectively, the Ministry and the Minister of Science and Higher Education.

29) “**Partnership**”shall mean a formal arrangement in which two or more parties cooperate to manage and operate an activity of mutual interest.

30) “**Patent**” means a title granted to protect inventions relating to a product or process that confers to its owner the rights recognized by the intellectual property laws of Ethiopia.

31) “**Person**” means natural or juridical person.

32) “**Plagiarism**” means claiming or insinuating ownership of another person’s intellectual and/or academic contribution; and it includes

a) using texts of another person without acknowledgement;
b) paraphrasing text without acknowledgement, or
c) using four or more words in the same form and sequence from acknowledged or unacknowledged source without quotation marks and specific page numbers.

33) “**Principal Investigator**” means an individual designated by a HEI or a funding organization to direct the project or program being supported by the fund.

34) “**Research**” means a systematized investigation to search for new knowledge or technology and/or to use existing knowledge or technology in a new and creative way in order to generate new concepts, methodologies, understandings, and to solve new or existing problems.

35) “**Research and Community Service Council**” means a governing body established to oversee research, community service and technology transfer activities.

ማለት ምርምርን፣ የማኅበረሰብ አገልግሎትንና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለመከታተል የተቋቋመ የአመራር/የአስተዳደር አካል ነው፡፡

፴፮) "**ለምርምር የተመደበ ገንዘብ**" ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለሚካሄድ ሣይንሳዊ የምርምር ፕሮጀክት፣ በኢንዱስትሪ፣ በፋውንዴሽን ወይም በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት የተደረገ የገንዘብ አስተዋጽዖ ነው፡፡

፴፯) "**የምርምር ሠራተኛ**" ማለት የአካደሚክ ሠራተኛ ሆኖ፣ ስድሣ በመቶ (60%) ጊዜውን ለምርምር ሥራዎች፣ ቀሪውን ጊዜ ደግሞ ለማስተማር፣ ተማሪዎችን ለማማከርና ለማኅበረሰብ አገልግሎቶች የሚያዉል ነው፡፡

፴፰) "**የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፓርክ**" ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ወይም ከሌሎች ተቋማት ጋር በአጋርነት የተገኙ የፈጠራ ምርቶችን ወይም የሥራ ሂደትን በማበልጸግ በዩኒቨርሲቲ፣ ኢንዱስትሪና መንግሥት መካከል ትብብርን ለማዳበር በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተዘጋጀና የሚመራ ፋሲሊቲ ነው፡፡

፴፱) "**ጅምር ንግድ/ኩባንያ**" ማለት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ጋር በተደረገ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት መሠረት በሠራተኞች ወይም በተማሪዎች ወይም በሌሎች ሰዎች የተመሠረተና በሥሪትና ግብይት ላይ የሚገኝ ቴክኖሎጂ ባለቤት የሆነ የንግድ ሥራ ነው፡፡

፵) "**የተማሪ ምርምር**" ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ወይም የምርምር ወጪን የሚሸፍን ድርጅት የምርምር ጭብጥ ዘርፎች በመከተል ለድህረ-ምረቃ ወይም ለመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት በከፊል ማሟያነት ተማሪዎች የሚያቅዱትና የሚያካሂዱት ምርምር ሲሆን፣ ከማናቸውም ወገን የገንዘብ ድጋፍ ቢገኝም፣ የአካዳሚክ ሠራተኛ ክትትል/ወይም የረዳት ክትትል ድጋፍ የሚሰጠው ነው፡፡

፵፩) "**የሠራተኛ ምርምር**" ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የአካዳሚክ ሠራተኞች በተቋሙ ወይም በሦስተኛ ወገን የገንዘብ ድጋፍ የሚሠሩት ምርምር ነው፡፡

፵፪) "**መምህር**" ማለት የአካዳሚክ ሠራተኛ ሆኖ፣ ስድሣ በመቶ (60%) ጊዜውን ለመማር-ማስተማር፣ ቀሪውን ጊዜ ደግሞ፣ ለምርምርና ለማኅበረሰብ አገልግሎት የሚያዉል ነው፡፡

፵፫) "**ቴክኖሎጂ**" ማለት ከምርምር ወይም ከፈጠራ

36) "**Research Grant**" means a financial contribution by an industry or foundation or governmental or non-governmental organization to a scientific research project conducted by a higher education institution.

37) "**Research Staff**" means an academic staff who spends 60% of his time to research activities, and the remaining time for teaching, student advising and community services.

38) "**Science and Technology Park**" means facility equipped and managed by a HEI designed to foster university, industry and government collaboration with the purpose of developing products or processes invented by or in partnership with higher education institutions.

39) "**Start-up Business/Company**" means a business created by staff or students or other individuals through a technology transfer agreement with a higher education institution which owns the technology being developed and marketed.

40) "**Student Research**" means research by students of higher education institutions designed and undertaken in line with the research thematic areas of the institutions or sponsoring organization for the purpose of partial fulfillment of the requirements of graduate or undergraduate degrees, supervised and/or co-supervised by academic staff member, regardless of the source of funding.

41) "**Staff Research**" means research done by academic staff through funding provided by the higher education institution or third parties.

42) "**Teaching Staff**" means an academic staff who spends 60% of his time to teaching-learning activities, and the remaining time for research and community services.

43) "**Technology**" means a product, process or knowhow of demonstrable benefit obtained through research or invention or imported or adapted from abroad, which could be disseminated or commercialized for public use.



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

የተገኘ ወይም ከውጭ አገር የተቀዳ ወይም ተወስዶ ማሻሻያ የተደረገበት ሆኖ፣ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የሚሰራጭ ወይም ለንግድ ሥራ ሊውል የሚችል፣ በምርምር የተረጋገጠ ወይም ግልጽ ጠቀሜታ ያለው ምርት፣ የምርት ሂደት ወይም የተግባር ዕውቀት ነው፡፡

፵፬) **"የቴክኖሎጂና ንግድ ሥራ ኢንክዩቤሽን ማዕከል"** ማለት አዲስ የንግድ ሥራዎች በምሥረታቸው ወቅትና በለውጥ ሂደታቸው እንዲበረታቱ፣ እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ ለማስቻል፣ አጠቃላይና ጉድኝት ያለው የኢንፍራስትረክቸር አገልግሎት፣ ኢንኩቤተር ሥፍራ፣ የንግድ ሥራ ድጋፍ አገልግሎት፣ የመሰባሰብ፣ እና የአውታረ-መረብ ዕድል እንዲያገኙ የሚያደርግ ማዕከል ነው፡፡

፵፭) **"የቴክኖሎጂ ሽግግር"** ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቴክኖሎጂን በነጻ ለሕዝብ ጥቅም ይውል ዘንድ ወይም በዓይነትና በመጠን ተገቢውን ክፍያ እያገኙ ኢንዱስትሪው ይበልጥ እንዲያሳድገውና ለገበያ እንዲያውለው የሚያስተላልፉበት ሂደት ነው፡፡

፵፮) **"ጭብጥ-ተኮር ምርምር"** ማለት ኅብረ-ጥናታዊና በተቀናጀ አኳኋን አካዳሚክ ሠራተኞችና ባለድርሻ አካላት ከተለያዩ የዕውቀት መስኮች ቅድሚያ ትኩረት በሚሹ አካባቢያዊና አገር አቀፍ ጉዳዮች ላይ ዘርፈ-ብዙ የምርምር ጭብጦችን በየፈርጁ በመመደብ የሚከናወን ጥናት ነው፡፡

፵፯) **"ዩኒቨርሲቲ"** ማለት በከፍተኛ ትምርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 መሠረት የተቋቋመ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፡፡

፵፰) **"ዩነቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር"** ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም እና/ወይም አካደሚክ ሠራተኞቹ ከኢንዱስትሪ ጋር ለጋራ ተጠቃሚነት የሚመሰርቱት የግንኙነት ስርዓት ነው፡፡ ይህም በጋራ ምርምር፣ በኮንትራት ምርምር፣ በምርምር የገንዘብ ምደባ፣ በምክር አገልግሎት፣ በማኅበረሰብ ተሳትፎ፣ በሠራተኛ ዝውውር፣ ለተማሪዎች ምርምር የጋራ ክትትል በማድረግ፣ በትምህርት ትብብር፣ ለኢንዱስትሪ ሠራተኞች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥልጠና በመስጠት፣ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ሠራተኞች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርት እንዲሰጡ በማድረግ ዕዉን ሊሆን ይችላል፡፡

፵፱) **"ምክትል ፕሬዚደንት"** ማለት የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራትን የሚመራ የዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚደንት ነው፡፡

44) **"Technology and Business Incubation Centre"** means a unit set up to nurture, accelerate and grow new businesses by providing comprehensive integrated support including infrastructure, incubator space, business support services and clustering and networking opportunities at early stage of development and change.

45) **"Technology Transfer"** means the transfer of technology by higher education institutions for public use for free , or to an industry for further development and marketing in exchange for appropriate type and amount of compensation.

46) **"Thematic Research"** means grouping of cross-cutting research problems in a multidisciplinary and integrated manner through the engagement of academic staff and stakeholders from different disciplines working on a similar range of issues in line with local and national priorities.

47) **"University"** means a higher education institution as defined by Higher Education Proclamation No. 1152/2019.

48) **"University-Industry Linkage"** means a system through which HEI and/or its academic staff interact with industry for mutual benefit. This can be realized through joint research, contract research, research grants, consultancy, community engagement, staff mobility, joint supervision of students, student internships, staff externships, co-operation in education, training of industry staff at higher education institutions and lecturing by industry staff.

49) **"Vice President"** means the Vice President of a university in charge of the university's Research, Technology Transfer, University-Industry Linkage and Community Service activities.

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ★ አዲስ አበባ ★ የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

**፬. <u>የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን</u>**

፩) ይህ መመሪያ ለሚኒስቴሩ በሕግ ተጠያቂ በሆኑ በሁሉም የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተፈፃሚ ነው፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተፈፃሚ ነው፡፡

፪) አግባብነት ያላቸው የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች፣ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት አዋጅ በሚገዙ የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ *በተመሳሳይ ሁኔታ* ተፈፃሚ ናቸው፡፡

**፭. <u>አጠቃላይ መርህ</u>**

፩) በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011፣ መሠረት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙበትን እውነታ ባገናዘበ ሁኔታ የአስተዳደር ሥርዓት ነፃነት ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሁሉም የወል ዓላማና ተልዕኮ ያላቸውና የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የሚያስተባብራቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በትብብርና በኅብረት ለመሥራት የሚያስችል የተቀናጀና የሚናበብ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲኖራቸው ስምምነት ያደርጋሉ፡፡

፪) ይህ መመሪያ ተግባራዊ የሚደረገው ለምርምር፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና ለማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራትና ለሚያስገኙት ጥቅም ምላሽና ትኩረት በሚሰጥበት አኳኋን ነው፡፡ በዚህ ረገድ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሴታና ለአካል ጉዳተኞች ትኩረትና ምላሽ የሚሰጡ ፕሮግራሞችን፣ ስትራተጂዎችን፣ እንዲሁም የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራትን በአጽንኦት ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

**4.** ***Scope of Application***

1) This Directive shall apply to all public higher education institutions which are legally accountable to the Ministry; and Article 4(2) of this provision shall apply to all private HEIs.
2) The relevant provisions of this Directive also shall *mutatis mutandis* apply to privately owned higher education institutions governed by the Ethiopian higher education law.

**5.** ***General Principle***

1) Taking into account that the HEIs Proclamation No. 1152/2019 gives autonomy to HEIs to have their own institutional governing system in line with their actual contexts, all HEIs, having a common goal and mission, shall agree to be coordinated by MoSHE to have integrated and harmonized governing system to work collaboratively and cooperatively.

2) This directive shall be applied in a way that is responsive and sensitive to different activities and benefits of research, technology transfer, university industry linkage and community services. To this end, HEIs shall strictly implement gender and disability sensitive and responsive programs, strategies, activities of research, TT, UIL and CS that enhance the participation of women and disabled staff and students.

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

# ክፍል ሁለት፡
# ምርምር

## ፮. ተቋማዊ የምርምር ፖሊሲዎችና መመሪያዎች

፩) ምርምርን በአግባቡ መምራት ይቻል ዘንድ፣ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጨምሮ፣ አጠቃላይ ተቋማዊ ፖሊሲዎችን የከፍተኛ ት/ ተቋማት ያዘጋጃሉ፤
   ሀ) የዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ ተሳትፎና ጥናታዊ ጉዞ፤
   ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረጉ ኮንፈረንሶች ተሳትፎ፤
   ሐ) የገንዘብ ማፈላለጊያ ወይም መመደቢያ ስልቶች፤
   መ) የምርምር ፕሮጀክቶች ገንዘብ አስተዳደርና አወጣጥ፤
   ሠ) ተቀባይነት ላገኙ የምርምር ውጤቶች ማበረታቻ የገንዘብ ክፍያ፤
   ረ) የምርምር ወይም የድህረ-ዶክቶራል ፌሎዎችን እና ተጋባዥ ስኮላሮችን መምረጥና መመደብ፤
   ሰ) ለምርምር ፕሮጀክት የተገዙ መሣሪያዎች ባለቤትነት፣
   ሸ) የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት፣
   ቀ) የምርምር ሥነምግባርና የሀቀኝነት ደንብ፤
   በ) የዳታ ማከማቻ ፤
   ተ) የማማከር አገልግሎት::

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምርምርን በሚመለከት ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትን ፖሊሲዎች ተግባራዊነት ለማረጋገጥ፣ እንዳስፈላጊነቱ አግባብነት ያላቸው ቅፆችን ያዘጋጃሉ፡፡

## ፯. የምርምርና ልማት ዕቅድ

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የራሳቸውን የምርምርና ልማት እንዲሁም የኢኖቬሽን ዕቅድ ያዘጋጃሉ፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምርና ልማት ዕቅድ በእውነት፣ በምክንያታዊነት፣ በአመክኖአዊ የሐሳብ ልውውጥና ችግር ፈቺ መርሆችዎች የሚመራ ሲሆን፣ በብሔራዊ ልማት ዕቅድ መሠረት ዘላቂ ማኀበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ተፈጥሮ አካባቢ (ኢኮሲስተም) ክብካቤ እንዲሁም ለኀብረተሰቡ ጥቅም የሚያስገኝ መሆን አለበት፡፡

፫) በምርምርና ልማት ዕቅዶች እንዲሁም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ዕቅዶች መሠረት፣ በዚህ መመሪያ በተመለከተው አኳኋን የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ክህሎትንና አቅም የሚያሳድግ ስትራቴጂ እንዲሁም ለምርምርና ልማት አግባብነት ያለው መዋቅር ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

# Part Two:
# Research

## 6. *Institutional Research Policies and Guidelines*

1) HEIs shall develop comprehensive institutional policies necessary to properly direct research, including policy on:
   a) Attendance of international conferences and study tours;
   b) Attendance of conferences in Ethiopia;
   c) Grant schemes;
   d) The administration and disbursement of funds for research projects;
   e) Financial motivation of researchers for accredited research outputs;
   f) The selection and appointment of research/postdoctoral fellows and visiting scholars;
   g) Ownership of equipment bought for research projects;
   h) Intellectual property;
   i) Code of research ethics and integrity;
   j) Data repository;
   k) Consultancy service.
2) HEIs shall where applicable develop standard forms that ensure compliance with the policies on research referred to under Sub-Article (1) of this Article.

## 7. *Research and Development plan*

1) HEIs shall develop their own research and development and innovation plan.
2) Research and development plan of higher education institutions shall be guided by the principles of truth, reason, rational discourse, and problem solving towards sustainable socio-economic development and ecosystem sustainability resulting in the benefits to the society in line with the National Development Plan.
3) Based on their research and development plans and other relevant plans, HEIs shall develop strategies for skills and potential development and appropriate structures for research and development support in accordance with this Directive.



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

## ፰. ጭብጥ-ተኮር ምርምርን በሚመለከት የምርምር ተግባራትና ቅድሚያ የሚሹ ክንውኖች፣

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የግንዛቤ ጥልቀትን የሚያስገኙና ኢኖቬሽንን የሚያነቃቁ መሠረታዊና ተግባራዊ ምርምሮችን ያካሂዳሉ፡፡

፪) በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚካሄዱ ምርምሮች በመርህ ደረጃ ጭብጥ ተኮር ይሆናሉ፣ የምርምር የጭብጥ መስኮች መሠረት የሚያደርጉት በአካባቢ፣ በክልል እና በብሔራዊ ደረጃ ቅድሚያ የሚሹ ጉዳዮችን ነው፡፡

፫) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በምርምር ተግባራቸው፣ በአካባቢ፣ በክልል እና በብሔራዊ ደረጃ ለምርምር አጀንዳ ውጤታማ ቴክኖሎጂን ለመፈለግ፣ ስለነርሱ ጥናት ለማድረግ፣ ለማሻሻል፣ ለመጠቀምና ለማሸጋገር ተግባራት ትኩረት ይሰጣሉ፡፡

፬) ለብሔራዊ፣ ለክልልና ለአካባቢያዊ ሁኔታዎች አስፈላጊ ከሆኑና ስኬታቸው ከፍተኛ አስተማማኝነት ካለው፣ ፈጠራ (ኢንቬንሽን) የሚያስገኙ ምርምሮች ተገቢው ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡

፭) የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የማኅበረሰቦችን ችግሮች ለመፍታት ተመራማሪዎች የአገር በቀል ዕውቀትን እንዲያሰባስቡ፣ እንዲያሳድጉና እንዲጠቀሙ ያበረታታሉ፡፡

፮) ብሔራዊ የምርምር አጀንዳን መሠረት በማድረግ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቅድሚያ የሚሹ ምርምሮችን በየዓምስት ዓመቱ ይለያሉ፡፡

፯) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር ጭብጥ-ተኮር ዘርፎችን የሚለዩት አንፃራዊ ጥንካሬአቸውንና ተነፃፃሪ ጥቅም መሠረት በማድረግ ነው፡፡

፰) በገንዘብ ምደባ መመዘኛዎች መሠረት ምክትል ፕሬዚደንቱ ለተተለሙት የምርምር ጭብጥ-ተኮር ዘርፎች በጀት ይመድባል፣ ውድድርን መሠረት በማድረግ የተመደበው ገንዘብ ለተመራማሪዎች እንዲለቀቅ ያደርጋል፡፡

## ፱. የሰራተኛና ተማሪ ምርምር

፩) የሠራተኛ ምርምር ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም የምርምር ጭብጥ-ተኮር ዘርፎች ጋር መጣጣም አለባቸው፡፡

፪) የድኅረ ምረቃ ተማሪዎች ምርምር ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ከተቋሙ የምርምር ጭብጥ-ተኮር ዘርፎች ጋር መጣጣም አለበት፡፡

፫) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፈር ቀዳጅ ግኝቶች ያሏቸውን ምርምሮች ያበረከቱ የድኅረ ምረቃ ተማሪዎችና ሠራተኞች ከምርምርና ልማት ወይም ከሌላ የገንዘብ ምንጭ ውድድርን መሰረት ያደረገ የማበረታቻ አሠራር ስርዓት ይዘረጋሉ፡፡

## 8. *Research activities and priorities regarding thematic research*

1) HEIs shall engage in both basic and applied research that deepen understanding and stimulate innovation.
2) Research at higher education institutions shall in principle be thematic in nature and shall identify research thematic areas based on local, regional and national priorities.
3) Higher education institutions, in their research undertakings, shall, as part of the local and national research agenda, focus on searching, learning about, adapting, and utilizing and transferring effective technologies.
4) Research leading to new inventions shall be given due attention particularly when it is highly feasible or is relevant to national, regional or local circumstances.
5) Higher education institutions shall encourage researchers to explore, enhance and utilize indigenous knowledge to solve the problems of communities.
6) Based on the national research agenda, higher education institutions shall set their research priorities every five years.
7) In the identification of thematic areas for research, higher education institutions shall be guided by their relative strength and comparative advantage.
8) The Vice President shall allocate budget for research thematic areas based on their funding criteria and disburse the funds to researchers on competitive basis.

## 9. *Staff and Student Research*

1) Research by staff shall be aligned with the HEI's research thematic areas.
2) Research by postgraduate students shall be aligned with the higher education institution's research thematic areas, for funding by the HEI.
3) Higher education institutions shall put in place incentive mechanisms through which postgraduate students and staff with breakthrough research findings could be rewarded on competitive basis from their research and development funds or other



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

፬) ተማሪና ሠራተኛ ተመራማሪዎች በቴክኖሎጂና የንግድ ሥራ ኢንክዩቤሽን ማዕከላት ተጠቅመው የምርምር ግኝቶቻቸውን ለገበያ ተፈላጊነት ወዳላቸው ምርቶች ይለውጧቸው ዘንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እገዛ ያደርጋሉ፡፡

**፲. <u>የድኅረ-ምረቃ ዶክተራል ፌሎውሺፕ መደቦች</u>**

፩) ጭብጥ-ተኮር የምርምር ፕሮጀክቶች የድኅረ-ምረቃ ዶክተራል ፌሎውሺፕን ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

፪) ከላይ የተመለከተው አንቀጽ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቅርብ ጊዜ የተመረቁ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን የፒኤች ዲ ምሩቃን ከአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ለመምረጥና ለመቀበል የድኅረ-ምረቃ ዶክቶራል ምርምር መደቦችን ያዘጋጃሉ፡፡

፫) ለድኅረ-ምረቃ ዶክተራል ምርምር መደቦች የገንዘብ ድጋፍ የሚደረገው ከመንግሥት በጀት፣ ከአገር ውስጥና ከዓለም አቀፍ የምርምር ገንዘብ ድጋፍ፣ ከስፖንሰሮች የገንዘብ ድጋፍ ወይም ለትብብር ምርምር ከተመደበ ገንዘብ ሊሆን ይችላል፡፡

**፲፩. <u>ተጋባዥ የምርምር ምሁራን</u>**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመስካቸው ከፍተኛ ከበሬታ ያተረፉ ምሁራንን በተጋባዥ የምርምር መደቦች ላይ እንዲሳተፉ ያበረታታሉ፤ ለዚህም በጊዜያዊነት ወይም በውል መሠረት ከውጭ ምንጮች የገንዘብ ድጋፍ ያፈላልጋሉ፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተጋባዥ ምሁራን በሚመለከት መመሪያ ያዘጋጃሉ፡፡

**፲፪. <u>ሴሚናርና ኮሎኪያ</u>**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችና ሠራተኞች ሥራዎቻቸውን በገለፃዎች፣ ሴሚናሮች እና ኮሎኪያ ለፐብሊክ የሚያቀርቡበት መርሃ-ግብር ይኖራቸዋል፡፡

፪) የድኅረ-ምረቃ ተማሪዎች ያላቸው የትምህርት ክፍል በዓመት ቢያንስ አንድ የድኅረ-ምረቃ ምርምር ሰሚናር መካሄድ አለበት፡፡

**፲፫. <u>ስትራተጂያዊ የምርምር ክላስተር</u>**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምርምርና ልማትን በሚመለከት ለመተባበር ተመሳሳይ የሆኑ የምርምር ፕሮግራሞች በመለየት የውስጠ-ተቋም ወይም በተቋሞች መካከል ስትራተጂያዊ የምርምር ክላስተሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ፡፡

**፲፬. <u>የምርምር ፈንድ እና ምንጮቹ</u>**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለምርምር ተግባሮቻቸው ገንዘብ የሚመድቡት ከመንግሥት በጀት፣ የአዕምሯዊ ንብረት መብቶቻቸውን ላይሰንስ

available fund.

4) Higher education institutions shall assist and advise student and staff researchers, through their Technology and Business incubation centers, to develop their research findings into marketable products.

**10. *Postdoctoral Fellowship Positions***

1) Thematic research projects may accommodate postdoctoral research fellowships.
2) Without prejudice to the foregoing provision of this Article, higher education institutions shall create postdoctoral research positions in order to select and host highly talented recent PhD graduates, nationals and foreigners.
3) Postdoctoral research positions may be funded by government budget, local or international research grants, research fund by sponsors or collaborative research fund.

**11. *Visiting Research Scholars***

1) Higher education institutions shall encourage scholars that are highly distinguished in their fields to take up visiting research positions with them by soliciting funding on ad hoc or contract basis from external sources.
2) HEIs shall develop a guideline on visiting scholars.

**12. *Seminars and Colloquia***

1) Higher education institutions shall have scheduled public events such as lectures, seminars and colloquia where students and faculty present their works to the public.
2) In academic units where there are postgraduate students, at least one annual graduate research seminar shall be held.

**13. *Strategic Research Clusters***

HEIs may establish intra- or inter-institutional strategic research clusters by identifying related research programs to collaborate and work towards research and development.

**14. *Research fund and sources***

1) HEIs fund their research activities through government budget and funds obtained from licensing of their intellectual property rights,



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

በማድረግ ከሚያገኙት ገንዘብ፣ ከትብብር የምርምር ፕሮጀክቶች፣ ከምርምር ስፖንሰርሺፕ፣ ለምርምር ከሚደርግ የገንዘብ ድጋፍ፣ ከኮንትራት ምርምር፣ ከማማከር አገልግሎትና ከሌሎች የገንዘብ ምንጮች ነው፡፡

፪) የፌዴራልና የክልል መንግሥታዊ አካላት እንዲሁም ሌሎች የፐብሊክ ምንጮች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የምርምር ፕሮጀክቶች በገንዘብ መደገፍ ወይም ስፖንሰር ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

፫) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሴትና ለወጣት ተመራማሪዎች ልዩ የገንዘብ ድጋፍ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡

## ፲፭. ብሔራዊ የከፍተኛ ትምህርት ምርምርና ልማት ፈንድ

ሚኒስቴሩ ብሔራዊ የከፍተኛ ትምህርት ምርምርና ልማት ፈንድ በማቋቋም ውድድርን መሰረት ያደረገ የምርምር በጀት ይመድባል፡፡ እንዲሁም አንገብጋቢ እና ትኩረት የሚሹ ከፍተኛ የአካባቢያዊ፣ ክልላዊ እና ሀገር-አቀፍ ችግሮችን ለመፍታት አካዳሚክ ሠራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም በትብብር የሚሰሩ ተመራማሪዎች ለሚያከናዉኗቸው ጥናቶች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

## ፲፮. የምርምር ፈንድ ስለማስተዳደር

፩) ምክትል ፕሬዚደንቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሙን የምርምር ፈንድንና ድጋፍ ያስተዳድራል፣ በየዓመቱ ያሳውቃል፡፡

፪) የተቋሙ የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ካውንስል የቀረበለትን የገንዘብ ድጋፍ ሐሳብ መርምሮ ያፀድቃል፡፡

፫) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻዎችን ጥራትና ሣይንሳዊ ፋይዳ ለማረጋገጥ የሚያስችላቸውን ሥርዓት ይዘረጋሉ፡፡

፬) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር ገንዘብ ድጋፍን የሚያስተዳድሩት ከድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ስለፈንድ አጠቃቀም ምንም ሳይገለጽ ለተቋማቱ ከሚሰጡ እንደ ርዳታ ከሚቆጠሩና ከከሌሎች ከተቋሙ ውጭ ከሚገኙ ፈንዶች በተለየ አኳኋን ነው፡፡

## ፲፯ የምርምር ገንዘብ ምደባ ጥያቄ የሚተዳደርበት የውስጥ መመሪያ

የምክትል ፕሬዚደንቱ ጽ/ቤት ለምርምር የገንዘብ ምደባ የሚቀርብ ጥያቄ የሚመራበትን ዝርዝር መመሪያ ያዘጋጃል፤ ከውስጥና ከውጭ ምንጮች የገንዘብ ድጋፍ የሚገኝበትን በሚመለከት አስፈላጊ ጉዳዮችን ይመራል፡፡

## ፲፰. የምርምር መጽሔት ላይ ለሚታተሙ ጽሁፎች ክፍያ

collaborative research projects, research sponsorship, research grants, contract research, consultancy service and other funding sources.

2) Federal and Regional state agencies and other public sources may fund or sponsor HEIs research projects.

3) HEIs shall avail special grant schemes for female and young researchers.

## 15. *National Higher Education Research and Development Fund*

The Ministry shall establish National Higher Education Research and Development Fund and allocate research budget on competitive basis; and it gives priority to studies by academic staff, students or collaborative researchers that relate to urgent and serious local, regional and national problems.

## 16. *Administration of Research Fund*

1) HEIs'research funds and grants shall be administered and announced annually by the Vice President.

2) The Institutional research and community service council shall review and endorse the proposal for grant support.

3) HEIs shall put in place mechanisms for ensuring the quality and scientific merit of grant applications.

4) HEIs shall treat research grants differently from other forms of external funds considered as donations to institutions from organizations or individuals without any specification as to how the fund can be utilized.

## 17. *Guidelines on Application for Research Grant*

The office of the Vice President shall prepare detailed guidelines that need to be followed by research grant applicants and regulate matters of importance for funding from internal or external sources.

## 18. *Journal Publication Fees*

1) HEIs may cover publication fees required by reputable journals for publication of articles.



አዲስ አበባ

፩) በስመ-ጥር/ ታዋቂ መጽሔቶች ላይ ለሚታተሙ የምርምር ጽሁፎች የሚጠየቀውን ክፍያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊሸፍኑ ይችላሉ፡፡

፪) ለማሳተሚያ ክፍያ የተጠየቀለት የምርምር ጽሁፍ ከክፍያ መጠይቁ ጋር ተያይዞ ለምክትል ፕሬዚደንቱ መቅረብ አለበት፡፡

## ፲፱. ፐብሊኬሽን፣ ዶኩሜንቴሽን እና ስርጭት

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሣይንሳዊ ዕውቀት ቋት(ኮርፐስ) አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፣ ይህን የሚያደርጉትም በፐብሊኬሽን፣ በሣይንሳዊ ስብሰባዎች ጥናቶችን በማቅረብ፣ የቀጣዩን ትውልድ ሣይንቲስቶችና ባለሙያዎች በማስተማርና በማሠልጠን እንዲሁም ዴታና ማቴሪያል በመጋራት ነው፡፡

፪) በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚካሄዱ ፐብሊኬሽኖችን የጥራት ደረጃዎች በሚመለከት ሀገር-አቀፍ መስፈርት ሚኒስቴሩ ያዘጋጃል፡፡

፫) በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚታተሙ አካዳሚክ መጽሔቶችን የስመ-ጥርነት/ታዋቂነት አነስተኛ መስፈርት ሚኒስቴሩ ያዘጋጃል፡፡

፬) ሚኒስቴሩ ስመ-ጥር/ታዋቂ መጽሔቶችንና የመጽሐፍት አሳታሚዎችን በምርምርና ቴክኖሎጂ ዴታቤዝ ያስገባል፡፡ ስመ-ጥር መጽሔቶችና የመጽሐፍት አሳታሚዎች ዝርዝር በየሦስት ዓመቱ ይከለሳል፣ ወቅታዊ ማስተካከያ ይደረግለታል፡፡

## ፳. የምርምር አቅም ግንባታ

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለአካዳሚክ ሠራተኞቻቸው፣ ለተማሪዎቻቸውና ለሌሎች ሠራተኞቻቸው አዕምሯዊ ክህሎትና አቅም የሚገነቡ ሥልጠናዎችን በየጊዜው ይሰጣሉ፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመራማሪዎቻቸው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በሚዘጋጁ ሳይንሳዊ ኩነቶች ላይ እንዲሳተፉ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

፫) በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን አዕምሯዊ ክህሎትና አቅም የመገንባት ተግባራት ለማከናወን ይቻል ዘንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፈንድ ይመድባሉ፣ ወይም የሚገኝበትን ሁኔታ ይሻሉ፡፡

፬) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማኅበረሰብ ልምድ እንዲለዋወጡና አቅማቸውን እንዲገነቡ ተቋማቱ በየጊዜው ሴሚናሮችንና ወርክሾፖችን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

፭) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሴትና ለወጣት ተመራማሪዎች ልዩ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ይነድፋሉ፣ ተፈፃሚም ያደርጋሉ፡፡

## ፳፩. የምርምር ክትትልና ግምገማ

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውጤታማና ቀልጣፋ የምርምር ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይቀይሳሉ፣ ተፈፃሚም ያደርጋሉ፡፡

2) The Vice President shall require that the copy of the article in question be attached to the requisition for payment of publication fee.

## 19. *Publication, Documentation and Dissemination*

1) HEIs are expected to contribute to the corpus of scientific knowledge through publications, presentations at scientific meetings, education and training of the next generation of scientists and professionals, and data and materials sharing.
2) The Ministry shall develop national level criteria on quality standards of publications at higher education institutions.
3) The Ministry shall in particular develop national minimum criteria for reputability of academic journals published at national and foreign institutions.
4) The Ministry shall enter the list of reputable journals and book publishers in its research and technology database. The list of reputable journals and book publishers shall be revised and updated every three years.

## 20. *Research Capacity building*

1) HEIs shall regularly organize relevant intellectual skills and capacity building trainings to their academic staff, students and other employees.
2) HEIs shall support their researchers to participate in national and international scientific events.
3) HEIs shall allocate or solicit funds to undertake the intellectual skills development activities outlined in this Article.
4) HEIs shall arrange regular seminars and workshops on which institutional community can share experiences and develop their capacity.
5) HEIs shall design and implement special capacity building programs for female and young researchers.

## 21. *Research Monitoring and Evaluation*

1) HEIs shall design and implement an effective and efficient Research monitoring and evaluation system.
2) HEIs shall endeavour to automate their



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለተመራማሪዎች ቀልጣፋ የምርምር አመራር እና ፍትሃዊ እንዲሁም አስተማማኝ አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችላቸው የምርምር አመራር ሥርዓታቸውን አውቶሜት ለማድረግ መጣር አለባቸው፡፡

፫) ምክትል ፕሬዚደንቱ አግባብነት ካላቸው የስልጠና መስኮች ብቃት ያለው የክትትል እና ግምገማ ቡድን ያቋቁማል፡፡ ይህ ቡድን የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

ሀ) የምርምር ሥራው በየደረጃው ያደረገውን ዕድገት መገምገም፣

ለ) እያንዳንዱ የተከናወነ ተግባር ለምርምሩ ዓላማዎች ስኬት ያለውን አግባብነት መመርመር፣

ሐ) በክወና ረገድ ያሉ ችግሮችን መለየትና እነዚህን ችግሮች ለመወጣት የመፍትሔ አስተያየት ማቅረብ፣

መ) በፀደቁ የምርምር ፕሮጀክቶች የተገለፁትን የምርምር ዘዴዎች ተመራማሪዎች በተገቢ ደረጃ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ፣

ሠ) በመጀመሪያው መርሀ-ግብር ወይም የተግባር ዕቅድ ላይ ማናቸውም ለውጥ ወይም ማሻሻያ የተደረገ መሆን አለመሆኑን፣ ይህ ተደርጎ ከሆነም ማብራሪያ የተሰጠ መሆኑን ማጣራት፣

ረ) የግብዓት (ሰው፣ የገንዘብ፣ የመገልገያ መሣሪያ፣ የመሠረተ ልማት እና የመጓጓዣ) አጠቃቀምን መገምገም፣

ሰ) የተባባሪ አባላትን የተሳትፎ መጠንና ክህሎት መገምገም፣

ሸ) የተከናወነውን ሥራ ጥራት መገምገም፣

ቀ) እንደአግባብነቱ፣ የሥነምግባር ደረጃዎች የተጠበቁ መሆናቸውን መገምገም፣

በ) በግልጽ የተመለከቱ ምክረ-ሐሳቦችን ማቅረብ፡፡

## ክፍል ሦስት
## የቴክኖሎጂ ሽግግርና ዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር

### ንዑስ ክፍል 1:- የቴክኖሎጂ ሽግግር

**፳፪. <u>የቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል መቋቋም</u>**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለተመራማሪዎች እና ለኢኖቬተሮች የቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል ያቋቁማሉ፡፡

**፳፫. <u>የአዕምሯዊ ንብረት መብቶች</u>**

፩) የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ አንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሠራተኛ በአገልግሎት ወይም በቅጥር ውሉ መሠረት፣ ወይንም ደግሞ የተቋሙን ንብረቶች፣ ዴታ፣ መገልገያዎች፣ ማቴሪያሎችና መሣሪያዎች ተጠቅሞ ያከናወነው የፈጠራ ሥራ

research management systems to provide efficient research management and put in place fair and reliable treatment of researchers.

3) The Vice President shall form a competent monitoring and evaluation team from relevant disciplines. The team shall perform the following tasks:

a. evaluate the progress made at each stage of the research;
b. examine the relevance of each activity undertaken to the fulfilment of the objectives;
c. identify operational problems and suggest solutions on how to overcome them;
d. make sure that researchers adhere to standard methodologies as specified in the research projects approved;
e. find out whether there are any changes or modifications to the original program or plan of action and whether these have been explained;
f. assess the utilization of resources (human, financial, equipment, infrastructure and transport) being made;
g. assess the degree of participation and skill of collaborating members;
h. assess the quality of work done;
i. assess if applicable whether ethical standards have been considered and
j. make specific recommendations.

## Part Three
## Technology Transfer and University- Industry Linkage

### Section 1 : Technology Transfer

**22. *Technology Data Centre Establishment***

HEIs shall establish technology data storage centre for researchers and innovators.

**23. *Intellectual Property Rights***

1) Unless agreed otherwise, an invention/ innovation created by an employee of HEIs in the execution of a contract of service or employment or by using the resources, data, means, materials or equipment of the



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

ወይም አዲስ አሠራር/ኢኖቬሽን ባለቤት ተቋሙ ነው፡፡

፪) በከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችና በሦስተኛ ወገን መካከል በተደረገ የትብብር ምርምር፣ ወይንም በሦስተኛ ወገን ስፖንሰርነት፣ ወይም በአገልግሎት ሥራ ወይም በምክር አገልግሎት የተገኘ የአዕምሮ ፈጠራ ወይም አዲስ አሠራር/ኢኖቬሽን ባለቤትነት የሚወሰነው የሚመለከታቸው ወገኖች በፈፀሙት ስምምነት መሠረት ነው፡፡

**፳፬. <u>የሠራተኞች የማሳወቅ ግዴታ</u>**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሠራተኞች በማናቸውም ጊዜና ሥፍራ የከወኑትን የአዕምሮ ፈጠራ ወይም ኢኖቬሽን ለተቋሙ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህ ግዴታ በተቋሙና በሠራተኞች መካከል የተደረገው የቅጥር ውል ስምምነት አካል ነው፡፡

**፳፭. <u>የቅድመ-ይፋነት መረጃ</u>**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሠራተኛ የአዕምሮ ፈጠራው ወይም ኢኖቬሽን ይፋ ከመደረጉ በፊት ለተቋሙ የቴክኖሎጂ ሽግግር ወይም አግባብነት ላለው ጽ/ቤት የቅድመ-ይፋነት መረጃ ያቀርባል፡፡ ይህም ምስጢራዊነቱ ሊጠበቅ የሚገባውን መረጃ አያካትትም፡፡

**፳፮. <u>ፈጠራ ወይም አዲስ አሠራር/ኢኖቬሽን ስለማሳወቅ</u>**

፩) አካዳሚክ ሠራተኛ የፓተንት ወይም የቅጅ መብት የሚያስገኝ ፈጠራ ወይም ኢኖቬሽን አግባብነት ላለው ጽ/ቤት በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

፪) ለተደረገው ፈጠራ ወይም ለኢኖቬሽን የሚቻለውን ሁሉ ጥበቃ ማድረግ ይቻል ዘንድ፣ በዚህ አንቀጽ፣ ንዑስ-አንቀጽ (1) የተመለከተው ተግባር የሚከናወነው ፈጠራውን ወይም ኢኖቬሽኑን ለፐብሊክ በይፋ ከማሳወቅ አስቀድሞ ነው፡፡

**፳፯. <u>ግምገማ</u>**

፩) ፈጠራ ወይም ኢኖቬሽን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 26(1) መሠረት ከተገለፀ በኋላ አግባብነት ያለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ጽ/ቤት ስለፈጠራው/ኢኖቬሽኑ አቅም፣ እንዳስፈላጊነቱም ፈጠራውን/ኢኖቬሽን ካገኘው ሰው ወይም የምርምር ቡድን መሪ ጋር በመሆን ፈጠራዉን/ኢኖቬሽኑን ይገመግማል፡፡

፪) በዚህ አንቀጽ፣ ንዑስ-አንቀጽ 1 የተመለከተው ግምገማ፣ የፓተንት መብት የሚያስገኝ መሆኑን፣ የኢኮኖሚ ጥቅም አቅሙን፣ በማኅበራዊና በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ያለውን ተጽዕኖ እንዲሁም የፈቃድ መጠይቅን ሊያውክ የሚችል ሌላ ሁኔታ መኖር አለመኖሩን ያካትታል፡፡

**፳፰. <u>ጥበቃን ስለመጠየቅ</u>**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የፓተንት ጥበቃ

Institution shall belong to the institution.

2) The ownership of intellectual property rights of invention/innovations resulting from collaborative research between a HEI and a third party or from a research sponsored by a third party or from a contract of service or consultancy work shall be regulated by the agreements between the concerned parties.

**24.** ***Employees' Obligation to Disclose***

Employees of HEIs shall disclose all invention/innovations made by them to the Institution, regardless of when or where the invention/innovations are made. This obligation shall be part of the contract of employment between the Institution and its employees.

**25.** ***Pre-Disclosure Information***

An employee of HEIs shall submit pre-disclosure information about the invention/innovation to the technology transfer or other relevant office of the Institution. The information should not include any confidential information.

**26.** ***Disclosure of Invention/innovation***

1) An academic staff shall disclose a patentable and copyrightable invention/innovation formally to the respective office.

2) In order to safeguard all the protection potentials of an invention/innovation, the disclosure referred to under sub-art (1) of this Article must be made before any public communication of the invention/innovation.

**27.** ***Evaluation***

1) Following the announcement of the invention/innovation referred to under Article 26(1) of this Directive, the respective office of the HEIs evaluates its potential together with, as the case may be, the inventor/innovator and the head of the research group.

2) The evaluation referred to under sub-art (1) of this Article includes patentability, economic potential, social and environmental impact, and any possible factors that may encumber licensing.

**28.** ***Seeking Protection***

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

ለሚያስፈልገው ፈጠራ ወይም ኢኖቬሽን የፓተንት ይሰጠኝ ጥያቄ ለሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ያቀርባሉ፤ የፓተንት መብቱን ፈቃድ ሂደት ይከታተላሉ፡፡

HEIs shall file application for patentable invention/innovation to the appropriate office of the government and follow up the patent process.

**፳፱. <u>ፈጠራን ለንግድ ሥራ መጠቀም</u>**

የፈጠራ ወይም ኢኖቬሽን ባለቤት የሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቴክኖሎጂውን ካገኘው ግለሰብ/ቡድን ጋር በመተባበር ፈጠራውን/ኢኖቬሽኑን ለማሳወቅና ለንግድ አገልግሎት ለማዋል የሚያስችሉ ተመራጭ መንገዶችን ይሻሉ፡፡

**29. *Commercialization***

HEIs that own a new invention/innovation shall, with the collaboration of the inventor/innovator of the technology, explore best ways of promoting and commercializing the invention/innovation.

**፴. <u>የምስጢር አጠባበቅ ስምምነት</u>**

የፓተንት ጥበቃ ያለውን ቴክኖሎጂ መጠቀም የሚያስችል ፈቃድ ለመስጠት ከሚደረገው የድርድር ሂደት ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ ከሚደረግ ድርድር አስቀድሞ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የፓተንት ፈቃድ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል ተብሎ በሚገመተው ወገን/ወገኖች መካከል የምስጢር አጠባበቅ ስምምነት ይደረጋል፡፡

**30. *Confidentiality Agreement***

Disclosure of the patentable technology to the potential licensees during the negotiation process or otherwise shall be preceded by a confidentiality agreement between the HEIs and such potential licensee or licensees.

**፴፩. <u>አዕምሯዊ ንብረትን የመጠቀም ፈቃድ ስለመስጠት</u>**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በሥራ ላይ ላሉ የንግድ ሥራዎች ወይም ለጅምር የንግድ ሥራዎች፣ የፈጠራ ወይም ኢኖቬሽን ፓተንት ተጠቃሚነት ፈቃድ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

፪) የፈጠራ/ኢኖቬሽን ተጠቃሚነት ፈቃድ ስምምነት የተዋዋይ ወገኖችን መብቶችና ግዴታዎች ይወስናል፡፡

**31. *Intellectual Property Licensing***

1) HEIs may license their invention/innovation to existing businesses or start-ups.
2) Licensing agreement shall regulate the rights and obligations of the parties.

**፴፪. <u>በብችኑነት ወይም ከሌሎች ጋር የመጠቀም ፈቃድ</u>**

፩) የፈጠራ/ኢኖቬሽን ተጠቀሚነት ፈቃድን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለአንድ ተጠቃሚ ብቻ ሊሰጡ የሚችሉ ሲሆን፣ ፈቃድ ተቀባዩ ቴክኖሎጂውን በብቸኝነት የመጠቀም መብት አለው፡፡

፪) በብቸኝነት የተሰጠ የተጠቃሚነት ፈቃድ ተቀባዩ ቴክኖሎጂውን ይበልጥ ማሻሻልና መጠቀም እንደሚችል ማመላከት አለበት፡፡

፫) በብቸኝነት የተሰጠ የተጠቃሚነት ፈቃድ ተቀባይ ፈቃዱን መልሶ እንዲያከራይ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

፬) ፈቃድ ሰጭው (የከፍተኛ ትምህርት ተቋም) በብቸኝነት ያልተሰጠን የተጠቃሚነት ፈቃድ ለሌሎች ወገኖችም የመፍቀድ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

፭) ስለፈቃድ አሰጣጥ ፈቃድ የተደረጉ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም ደግሞ እንደሁኔታው ሚኒስቴሩ ወይም ሌሎች የመንግሥት ተቋማት፣ በግዥ ረገድ

**32. *Exclusive or Non-Exclusive License***

1) HEIs may grant a licensee an exclusive license in which case the licensee is granted a monopoly on the exploitation of the technology.
2) Exclusive license shall indicate that the licensee will further develop and exploit the technology.
3) An exclusive license may grant the licensee the right to sublicense it.
4) A license may be a non-exclusive one in which case the licensor (the HEI) reserves the right to grant licenses to other parties.
5) The contrary provisions of the licensing agreements notwithstanding, the HEIs and, as the case may be, the Ministry or other government institutions shall be granted a

ከሮያልቲ ክፍያ ነፃ የሆነና ከሌሎች ጋር የሚጠቀሙበት ፈቃድ ይሰጣቸዋል፡፡

**፴፫. <u>መልሶ የመውሰድ መብት</u>**

ፈጠራን/ኢኖቬሽንን እንዲጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ሰው ቴክኖሎጂውን የሚያሳድጉ ወይም በሙሉ ጥቅም ላይ የሚያውሉ ውጤታማ እርምጃዎችን ካልወሰደ፣ ወይም ለጤና/ለደህንነት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወይም መንግሥት የሰጠውን ፈቃድ መልሶ የመውሰድ መብቱ ተጠብቆ፣ የፈጠራ/ኢኖቬሽን መጠቀም ፈቃዱን ለሦስተኛ ወገን ለመስጠት ወይም ደግሞ ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም ቴክኖሎጂው እንዲያድግና ለንግድ ሥራ እንዲውል ያደርጋል፡፡

**፴፬. <u>በስፋት ስለማምረት</u>**

የፈጠራ/ኢኖቬሽንን ፈቃድ በኢትዮጵያ ውስጥ በብቸኝነት እንዲጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ሰው፣ በሀገር ውስጥ ያለው የማምረት አቅም በፈቀደለት መጠን፣ ፈቃድ ያገኘበትን ምርት በስፋት ለማምረት መስማማት አለበት፡፡

**፴፭. <u>የመከወን ግዴታ</u>**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቴክኖሎጂን ስለመጠቀም ፈቃድ በሚሰጡበት ጊዜ፣ ፈቃድ ተቀባዩ ቴክኖሎጂውን በማሳደግ ወደገበያ እስኪገባ ድረስ የተቻለውን ሁሉ ጥረት እንደሚያደርግ ወይም ይህ ካልሆነ የንግድ ሥራ ቃሉን እንዳላከበረ እንደሚቆጠርና፣ በዚሁ ምክንያት የፈቃድ ሥረዛን ጨምሮ እንደሁኔታው ካሣ ሊጠየቅ እንደሚችል ተቋማቱ ለፈቃድ ተቀባዩ በጽሁፍ ግዴታውን ይገልፁለታል፡፡

**፴፮. <u>ማቴሪያልን የማስተላለፍ ስምምነት</u>**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለምርምርና ለልማት ተግባራት የሚውሉ የምርምር ማቴሪያሎችን ለማግኘት ይችሉ ዘንድ ከሌሎች የምርምር ተቋማት ወይም ከኢንዱስትሪ ጋር ማቴሪያልን የማስተላለፍ ስምምነት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

፪) የሰው ባዮሎጂክ ማቴሪያል እና ናሙናዎችን እንዲሁም ለሰዎች አካል ጥቅም ላይ የሚውሉ ማቴሪያሎችን በሚመለከት ተፈጻሚ የሚሆኑት ስለክሊኒካል ሙከራዎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያወጧቸው ልዩ ደንቦች ናቸው፣ ደንቦቹም የሚወጡት በዓለም አቀፍ ልምድና በአገሪቱ ተግባራዊ በሆኑ ሕጎች መሠረት ነው፡፡

**፴፯. <u>ገቢ</u>**

ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ፈቃድ በመስጠት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያገኙት ገቢ በተሸጡ ምርቶች ወይም በአገልግሎቶች ላይ የሚከፈል ሮያልቲ፣ ፈቃድን መልሶ በማከራየት የሚገኝ ሮያልቲ፣ ቀጥተኛ

royalty free non-exclusive license for procurement purpose.

**33. *March-in Rights***

In the event that the licensee fails to take effective steps to develop or exploit the technology, or if doing so is necessary to meet health or safety needs, the licensing HEI or the government retains march-in rights to cause third party licensing or undertake other options to realize the development or commercialization of the technology.

**34. *Substantial Manufacture***

If an exclusive license of an invention/innovation is granted in Ethiopia, the licensee must agree to substantially manufacture the licensed product within Ethiopia as far as the capacity to do that exists in the country.

**35. *Performance Obligation***

In granting license to use technology, HEI shall require in writing that the licensee assumes the obligation to make best efforts to develop and utilize the technology until either it reaches the market or otherwise fails to fulfil its commercial promise and that failure to do so shall result in measures including revocation of the license agreement with the right to claim damages if applicable.

**36. *Material Transfer Agreements***

1) HEIs may enter into material transfer agreements with other research institutions or the industry in order to obtain research materials for the purpose of research and development activities.
2) The transfer of human biologic material and specimens and materials for use in humans shall be governed by special regulations pertaining to clinical trials to be developed by HEI based on acceptable international practice applicable to laws of the country.

**37. *Revenue***

The Revenue HEIs obtain from licensing their technologies may be in the form of royalties on the products or services sold; royalties on sub-licenses; up-front payments; annual payments; or stock or



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

ክፍያ፣ ዓመታዊ ክፍያ፣ ወይም አዲስ ኩባንያ ሲቋቋም የአክሲዮን ድርሻ በማግኘት ሊሆን ይችላል፡ ይህም የሚወሰነው ተቋማቱ ከፈቃድ ተቀባዩ ጋር ተደራድረው በሚደርሱበት ስምምነት መሠረት ነው፡፡

**፴፰. ገቢን ስለመጋራት**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከፈጠራ ሥራ ከሚያገኙት ገቢ ላይ ለፓተንት እና ፈጠራውን ለማሳደግ የተደረጉት ወጭዎች ከተቀነሱ በኋላ፣ ቀሪው በፈጠራው አመንጭ/ዎች፣ ፈጠራው በተካሄደበት አካዳሚክ ዩኒት ወይም ቤተ-ሙከራ፣ እና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካከል ይከፋፈላል፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሚያወጡት የውስጥ መመሪያ መሠረት የእያንዳንዱ ወገን የክፍያ ድርሻ የሚወሰን ሲሆን፣ ይህም የሚወሰነው የሌሎች አገሮችን የአሠራር ዘዴ ከግምት በማስገባት ነው፡፡

፫) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አግባብነት ላላቸው ለተቋሙ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ማበረታቻ ይሰጣሉ፣ ይህን የሚያደርጉት ለንግድ ሥራ ሊውሉ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን ዕድገት ለማሳካትና ሌሎች የፐብሊክ ጥቅሞችን ለማስገኘት ነው፡፡

፬) የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የፈጠራ ሥራው እድገት ስለሚገኝበት ሁኔታ ለሚኒስቴሩ፣ ወይም እንደሁኔታው ለሌሎች ፈንዲንግ ተቋማት በየዓመቱ ሪፖርት ያቀርባሉ፡ ይህም ሪፖርት የፈጠራ ሥራውን ለንግድ ሥራ በማዋል የተገኙትን ሮያልቲና ሌሎች ገቢዎች ይጨምራል፡፡

**፴፱. ጅምር ኩባንያዎች**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በትምህርት ክፍሎቻቸው ወይም በቤተ-ሙከራዎቻቸው በተደረገ ምርምር የተገኙትን ቴክኖሎጂዎች ለማሻሻልና ለንግድ ሥራ እንዲውሉ ለማድረግ የሚሹ ጅምር ኩባንያዎች እንዲቋቋሙ ያበረታታሉ፣ ይህም የሚደረገው የርስ በርስ ግምገማ በመሳሰሉና እንደሁኔታውም ውድድርን መሠረት ባደረገ ፕሮጀክት-ተኮር የገንዘብ ድጋፍ እና መነሻ ገንዘብ በመመደብ ነው፡፡

፪) ጅምር ኩባንያ የተጠቃሚነት ፈቃድ ማግኘት ይችል ዘንድ ፈቃድ የሚጠይቅበትን የፈጠራ ሥራ/ኢኖቬሽን ወይም ቴክኖሎጂ ለንግድ ሥራ ለማዋል የሚያስችለውን ዕቅድ ማቅረብ አለበት፡፡

፫) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሠራተኞቻቸው፣ ተማሪዎቻቸውና ሌሎች የፈጠራ አመንጭዎች ጅምር ኩባንያ በተቋሞቹ የኢንኩቤሽን አገልግሎቶች አማካይነት እንዲያቋቁሙ ይደግፋሉ፣ የስራ ፈጠራ ምክርም ይሰጣሉ፡፡

share in the start-up companies based on the negotiated agreements they make with the licensee.

***38. Revenue-Sharing***

1) Revenues obtained by HEIs from their invention/innovations shall, after the deduction of the patent and other development costs, be shared among the inventor (inventors), the academic unit or laboratory where the invention/innovation was made and the HEIs.
2) HEIs shall by their internal rules determine the amount due to each of the receivers taking into account modalities used in other jurisdictions.
3) HEIs shall determine and provide incentives for appropriate officials and staff in the institutions in order to encourage them to effectively develop technologies with commercial potentials or other public benefits.
4) HEIs shall report annually to the Ministry or, as the case may be, to other funding agencies on the development status of invention/innovations, including royalties or other payments received from commercialization of the invention/innovation.

***39. Start-Up Companies***

1) HEIs shall, through peer-reviewed, and as the case may be, competitively allocated project-specific grants and seed money, encourage the creation of start-up companies that wish to develop and commercialize the technologies emanating from the research done in their laboratories or academic units.
2) A start-up company must offer a viable plan to commercialize an invention/innovation or a technology in order to receive a license.
3) HEIs shall support their staff, students and other inventors to launch start-up companies through their incubation services and shall give entrepreneurial advices.

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
ሪከርድና ማህደር አገልግሎት

## ንዑስ ክፍል 2- የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር

**፵. <u>አጋርነት</u>**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አንድ ለአንድ በሆነ ግንኙነት ወይም በቅንጅት አማካይነት የምርምር፣ የማማከር አገልግሎት፣ የሠራተኛ ልውውጥ፣ የኢንተርንሺፕ/ኤክስተርንሺፕ አጋርነትን ከኢንዱስትሪ ጋር ይመሠርታሉ፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በትብብር ወይም በስፖንሰርነት በሚካሄዱ ምርምሮች ይሳተፋሉ፣ እንዲሁም የተቋሞቹን የኤክስፐርት አቅም መጠቀም ይቻል ዘንድ ፈንድና ገበያን በመሻት አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡

፫) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ኢንዱስትሪዎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በመለየት ኢንዱስትሪዎችን ለመርዳት ጭብጥ-ተኮር አቅጣጫዎችን ይወስናሉ፡፡

፬) ከኢንዱስትሪው ጋር የምርምር ወይም የአገልግሎት ትብብር ስምምነት ውስጥ ይገቡ ዘንድ፣ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የትምህርት ክፍሎቻቸውን ያበረታታሉ፡፡

፭) በምርምርና በአገልግሎት ትብብር ረቂቅ ዝግጅትና ድርድር ረገድ፣ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለአካዳሚክ ሠራተኞቻቸው ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

፮) የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር መድረክ እንዲመሠረትና ዘላቂነት እንዲኖረው፣ ከኢንዱስትሪውና በሚገኙበት ክልል ከሚገኙ ሌሎች ተቋማት ጋር በመሆን ጉልህ ሚና ይጫወታሉ፡፡

**፵፩. <u>የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ የምርምር ማዕከላት</u>**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ኢንዱስትሪ በቅንጅት የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ የምርምር ማዕከላትን ያቋቁማሉ፤ ማዕከላቱ ለተለዩ የሳይንስ መስኮች ምርምርና ልማት፣ ለምርምር ክላስተር ወይም ሌላ ሊተገበር ለሚችል ምርምርና ልማት ሥራዎች ማዕከል ሆነው ያገለግላሉ፡፡

፪) የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ የምርምር ማዕከላት ሥራቸውን የሚያከናውኑት ከዚህ በታች በአንቀጽ 42 በተመለከተው የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር የሥራ ቡድን አማካይነት ነው፡፡

**፵፪. <u>የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር የሥራ ቡድን</u>**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር የሥራ ቡድን ያቋቁማሉ፡፡

፪) የሥራ ቡድኑ ቅድሚያ የሚሹት ቴክኖሎጂዎችን ይለያል፡፡

፫) በእያንዳንዱ የሥራ ቡድን የሚሳተፉት አጋሮች የትብብር ስምምነት ይፈርማሉ፡፡

## Section 2: University-Industry Linkage

**40.** ***Partnership***

1) HEIs shall create research, consultancy, staff exchange, internship/externship partnerships with industry on one-to-one or consortia basis.
2) HEIs shall engage in collaborative or sponsored research partnerships, and facilitate funding for and marketing of the expertise of the institutions.
3) HEIs shall identify problems encountered by industries to set thematic areas to support industries.
4) HEIs shall encourage their academic units to enter into research or service cooperation agreements with the industry.
5) HEIs shall support academic staff in drafting and negotiating research and service contracts.
6) HEIs shall play active roles together with the industry and other institutions in the regions in which they are located to create and sustain UIL forum.

**41.** ***University-Industry Research Centers***

1) HEIs and industry may, in consortia, establish University-Industry Research Centres which serve as research and development hubs for partnerships in relation to specific scientific fields, research clusters or such other practicable research and development activities.
2) The University-Industry Research Centres shall function through University-Industry Linkage Working Team referred to in Article 42 here in below.

**42.** ***University-Industry Linkage Working Team***

1) HEI shall establish University-Industry Linkage Working Team.
2) The working team shall identify the technologies that need to be prioritized.



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

፬) ፕሮጀክቶቹ ተግባራዊ የሚደረጉበት የሥራ ሥፍራ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ቤተሙከራዎች ወይም በዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ የምርምር ማዕከላት የሚሳተፉ አጋሮች ያቋቋሚቸው የቴክኖሎጂ ፓርኮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## ክፍል አራት
## የማኅበረሰብ አገልግሎት

**፵፫. <u>የማኅበረሰብ አገልግሎት መምሪያ</u>**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የራሳቸውን የማኅበረሰብ አገልግሎት መምሪያ ያዘጋጃሉ፡፡

**፵፬. <u>የማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራትና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች</u>**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

፩) የሥልጠና አገልግሎት
፪) የማማከር አገልግሎት
፫) የአውትሪች/ልማት አገልግሎት/ፕሮጀክቶች
፬) ሌሎች ሙያዊ አገልግሎቶች፡፡

**፵፭. <u>ጭብጥ-ተኮር የማኅበረሰብ አገልግሎት</u>**

፩) የማኅበረሰብ አገልግሎት ጭብጥ-ተኮር የትኩረት አቅጣጫ ይኖረዋል፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካባቢያዊና አገራዊ የቅድሚያ ትኩረት አቅጣጫዎችን መሠረት በማድረግ የማኅበረሰብ አገልግሎት ጭብጥ-ተኮር መስኮችን ይወስናሉ፡፡

ሀ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካዳሚክ ሠራተኞች ምርምሮቻቸውን ወይም የቴክኖሎጂ ውጤታቸውን ለማኅበረሰቡ ያቀርባሉ፡፡

ለ) የማኅበረሰብ ችግሮችን ለመፍታት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካዳሚክ ሠራተኞች ሀገር-በቀል ዕውቀትን ያሰባስባሉ፣ ያሳድጋሉ፣ ይጠቀማሉ፡፡

ሐ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የማኅበረሰብ አገልግሎት የትኩረት መስክ የሚወሰነው ባላቸው አንፃራዊ ጥንካሬና ንጽጽራዊ ጠቀሜታ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

መ) የገንዘብ ምደባ መመዘኛዎችን መሠረት በማድረግ፣ ምክትል ፕሬዚደንቱ ለማኅበረሰብ አገልግሎት ጭብጥ-ተኮር መስኮች የሚያስፈልገውን በጀት ይመድባል፣ በተወዳዳሪነት ላይ ተመሥርቶ የተመደበውን ገንዘብ ለአካዳሚክ ሰራተኛ ይፈቅዳል፡፡

3) Partners participating in each of the working team shall sign an agreement of collaboration.
4) The work station for the implementation of the projects may be in the HEIs laboratories or technology parks of the participating partners of the university-industry research centres.

## Part Four
## Community Service

**43. *Community Service Guideline***

HEIs shall develop their own community service guideline.

**44. *Community Service Activities and Priorities***

The Community Service activities of HEIs shall include

1) Training service
2) Consultancy service
3) Outreach/development service/projects
4) Other professional services

**45. *Thematic Community Service***

1) Community Service shall be thematic.
2) HEIs shall set community service thematic areas based on local and national priorities.
   a) HEIs' academic staff shall deliver their research or technological outputs to the community.
   b) HEIs academic staff shall explore, enhance and utilize indigenous knowledge to solve the problems of communities.
   c) Thematic area identification shall be guided by the relative strength and comparative advantage of HEIs.
   d) The Vice president shall allocate budget for community service thematic areas based on their funding criteria and disburse the funds to the academic staff on competitive basis.

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
ሪከርድና ማህደር አገልግሎት

**፵፮. <u>የማኅበረሰብ አገልግሎት አፈፃፀም፡- የማኅበረሰብ አገልግሎት ቡድን</u>**

፩) የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለእያንዳንዱ የማኅበረሰብ አገልግሎት መስክ፣ የማኅበረሰብ አገልግሎት ቡድን እንዲመሠርቱ ይበረታታሉ፡፡

፪) የማኅበረሰብ አገልግሎት ቡድን ቢያንስ ሦስት የአካዳሚክ ሠራተኞች እና/ወይም ተማሪዎችን በአባልነት ሊይዝ ይችላል፡፡

፫) በዚህ አንቀጽ መሠረት የተቋቋመው ቡድን አንድ የቡድን መሪ ይኖረዋል፡፡

፬) የማኅበረሰብ አገልግሎት ቡድን መሪ የገንዘብ ድጋፍ አድራጊ ተቋማት መመሪያዎች፣ እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገንዘብ አስተዳደርና አወጣጥ መመሪያዎች በጥንቃቄ ተግባራዊ የተደረጉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

# ክፍል አምስት
# አስተዳደር፣ ሥነ-ምግባር፣ ደረጃዎች፣ መርሆዎችና ግብዓቶች

## ንዑስ ክፍል 1- አስተዳደር

**፵፯. <u>የከፍተኛ ትምህርት ምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ካውንስል</u>**

፩) ሚኒስቴሩ የከፍተኛ ትምህርት ምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ካውንስል ያቋቁማል፡፡

፪) የካውንስሉ ሰብሳቢ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ሆኖ ካውንስሉ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚደንቶች፣

ለ) የግል ዩኒቨርስቲዎች ፕሬዚደንቶች፣

ሐ) የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማኅበር ፕሬዚደንት፣

መ) የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ኃላፊ፣

ሠ) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ኢንስቲትዩት ኃላፊ፣

ረ) በሚኒስቴሩ የሳይንስ፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግት ዳይሬክተር ጀነራል፣ የካዉንስሉ ፀሐፊ፣

ሰ) የኢትዮጵያ ሲቪስ ሰርቪሸ ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚደንት፣

ቀ) የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ምርምርና

**46. *Implementation of Community Service: Community Service Team***

1) HEIs are encouraged to form Community Service Team for each Community service activities.
2) The Community Service Team shall be composed of minimum of three academic staffs and/or students
3) The Team established under this article shall have a Team Leader.
4) The Community Service Team Leader is responsible to ensure the funding agencies' guidelines as well as the guidelines on the management and disbursement of funds provided by the HEIs is followed scrupulously.

# Part Five
# Governance, Ethics, Standards, Principles and Resources

## Section 1: Governance

**47. *Higher Education Research and Community Service Council***

1) The Ministry shall establish Higher Education Research and Community Service Council.
2) The Council shall be chaired by the State Minister of Science and Higher Education and shall have the following members:
   a) Research and Community Service Vice Presidents of Public Higher Education Institutions;
   b) Presidents of Private Universities;
   c) President of Private Higher Education Institutions Association;
   d) Head of Federal Technical and Vocational Education and Training Agency;
   e) Head of Technical and Vocational Education and Training Institute;
   f) The Science, Research and Community Service Director General of the Ministry, Secretary of the Council;
   g) Research and Community Service Vice President of Ethiopian Civil Service University;



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚደንት፤
በ) የፌዴራል መከላከያ ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚደንት፤
ተ) የኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚደንት፤
ቸ) የፌዴራል ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚደንት፡፡

፫) ካውንስሉ ሥልጣኑና ተግባሩን እንዲሁም የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ደንቦቹንና ሥነሥርዓቶቹን በሚመለከት ሰነድ ያዘጋጃል፣ በሚኒስትር ዲኤታው ሲፀድቅ ተፈፃሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

፬) ካውንስሉ በየሩብ ዓመቱ ይሰበሰባል፡፡

**፵፰. ተቋማዊ የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ካውንስል**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተቋማዊ የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ካውንስል ይኖራቸዋል፡፡

፪) ምክትል ፕሬዚደንቱ የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ካውንስሉ ሰብሳቢ ሆኖ ካውንስሉ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-
ሀ) የምርምርና ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ፤
ለ) የማኅበረሰብ አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊ፤
ሐ) የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ጽ/ቤት ኃላፊ፤
መ) የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ተባባሪ/ረዳት ዲን፣ ወይም አግባብነት ያለው የእያንዳንዱ አካደሚክ ዩኒት ኦፊሰር፡፡

፫) ካውንስሉ የራሱ መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፡፡

**፵፱. የትምህርት ክፍል ምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ካውንስል**

፩) እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ካውንስል ይኖረዋል፡፡

፪) የካውንስሉ ሰብሳቢ የትምህርት ክፍሉ ምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ረዳት/ተባባሪ ዲን ወይም አግባብነት ያለው ኦፊሰር ነው፡፡

፫) እያንዳንዱ ትምህርት ክፍል እንደአግባብነቱ የካውንስሉን አባላት ይመርጣል፡፡

**፶. ድርጅታዊ አወቃቀር**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራትን በቀልጣፋና ውጤታማ ሁኔታ ለማከናወን አመቺ የሆኑ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅሮችን ይዘረጋሉ፡፡

፪) የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራትን ምክትል ፕሬዚደንቱ ይመራል፡፡

፫) ከዚህ በታች የተመለከቱት ተጨማሪ ጽ/ቤቶች ተጠሪነታቸው ለምክትል ፕሬዚደንቱ ሲሆን፣ እንደ

h) Research and Community Service Vice President of Kotebe Metropolitan University;
i) Research and Community Service Vice President of Federal Defence University;
j) Research and Community Service Vice President of Oromia State University;
k) Research and Community Service Vice President of Federal Police University College.

3) The Council shall formulate and, upon approval by the Sate Minister, implement its powers and functions as well as its meeting and decision-making rules and procedures.

4) The council shall meet on quarterly basis.

***48. Institutional Research and Community Service Council***

1) HEIs shall have institutional Research and Community Service Council.
2) The Research and Community Service Council shall be chaired by the Vice President and shall have the following members:
   a) Research and Development Office Head;
   b) Community Service Office Head;
   c) UIL-TT Office Head;
   d) Research and Community Service associate/vice dean/ or related officer/coordinator of each academic unit.
3) The Council shall formulate its own governing document.

***49. Academic Unit Research and Community Service Council***

1) Each Academic Unit shall have Research and Community Service Council.
2) The council shall be chaired by the respective RCS Vice/associate dean or related officer.
3) Each Academic Unit shall choose the members of the council as appropriate.

***50. Organizational Structure***

1) HEIs shall put in place organizational and administrative structures that are conducive for efficient and effective execution of research, Technology Transfer, University-Industry linkage and Community Services activities.
2) The Vice President shall lead research,

የከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ ሁኔታ ይቋቋማሉ፡-

ሀ) የምርምርና ልማት ጽ/ቤት፣
ለ) የፐብሊኬሽንና ዶኪዩመንቴሽን ጽ/ቤት፣
ሐ) የማኅበረሰብ አገልግሎት ወይም ኢንጌጅመንት ጽ/ቤት፣
መ) የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ጽ/ቤት፣
ሠ) የድኅረ ምረቃ ተማሪዎች ምርምር ጽ/ቤት፣
ረ) የአጋርነትና የምርምር የውጭ ፈንድ ጽ/ቤት፣

፬) ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱት ጽ/ቤቶች አስፈላጊው የሰው ኃይል ይኖራቸዋል፣ የሠራተኛ ምደባ የሚደረገውም ችሎታን መሠረት ባደረገ የውድድር መስፈርቶች መሠረት ነው፡፡

፭) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተጠሪነቱ ለምክትል ፕሬዚደንት የሆነ ተቋማዊ የሥነ-ምግባር ግምገማ ቦርድ ይኖራቸዋል፡፡

፮) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተጠሪነቱ ለምክትል ፕሬዚደንት የሆነ ተቋማዊ የአዕምሯዊ ንብረት መብቶች ቦርድ ይኖራቸዋል፡፡

፯) የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራትን በሚመለከት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርት ክፍሎች ተጠሪነታቸው ለምክትል ፕሬዚደንቱ ነው፡፡

## ፶፩. የምክትል ፕሬዚደንቱ ተግባርና ኃላፊነት

፩) የምክትል ፕሬዚደንቱን ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም በውስጠ ደንባቸው መሠረት በምክትል ፕሬዚደንቱ ሥር የሚመሩ ጽ/ቤቶችን፣ የከፍተኛ ት/ተቋም ፕሬዚደንት በግልጽ ለይቶ ያመለክታል፡፡

፪) የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራትን በሚመለከት የትምህርት ክፍሎች ሪፖርት የሚያቀርቡት ለምክትል ፕሬዚደንቱ መሆኑን፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፕሬዚደንቶች ያረጋግጣሉ፡፡

፫) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ምክትል ፕሬዚደንት፡-

ሀ) የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ዕቅዶችንና ፖሊሲዎችን ያዘጋጃል፣ ያስፈጽማል፤
ለ) የምርምር ጭብጥ-ተኮር አቅጣጫዎች ተለይተው የታወቁ መሆናቸውንና በየጊዜውም ወቅታዊ የተደረጉ መሆኑን ያረጋግጣል፤
ሐ) የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራት እና የድጋፍ ሥርዓቶች በትክክል የሚሠሩ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

technology transfer, university-industry linkage and community service activities.

3) The following subsidiary offices that are accountable to the Vice President shall be established as per the context of the HEIs:
   a. Research and Development Office,
   b. Publications and Documentation Office,
   c. Community Service and/or Engagement Office,
   d. University-Industry Linkage and Technology Transfer Office,
   e. Postgraduate Students' Research Office,
   f. Partnership and External Research Fund Office.
4) The offices referred to under Sub-Article (3) of this Article shall have the necessary staff recruited and appointed on the basis of meritorious competition criteria.
5) HEIs shall have Institutional Ethical Review Board accountable to the Vice President.
6) HEIs shall have Intellectual Property Rights Board accountable to the Vice President.
7) Academic units of HEIs shall be accountable to the Vice President in regards to their research, technology transfer, university-industry linkage and community services activities.

## 51. *Powers and Functions of the Vice President*

1) The President of HEIs shall delineate the powers and functions of the Vice President and offices under his/her remit in their internal legislation.
2) Presidents of HEIs shall ensure that academic units report to the Vice President concerning research, technology transfer, university-industry linkage and community service
3) Notwithstanding the provisions of Sub-Art (1) of this Article, the Vice President of a higher education institution shall:
   a. develop and implement the institution's research, technology transfer, university-industry linkage and community service plans and policies;
   b. make sure that research thematic areas are



አዲስ አበባ

መ) የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት የፋይናንስ አስተዳደርና፣ ግዥ እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎትን በሚመለከት የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ያደርጋል፣

ሠ) ለቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራት አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፣ ቴክኖሎጂን ለማፍለቅ የሚያስችሉ ምርምሮችን የሚሰሩ ተመራማሪዎችን ያስተባብራል፣ ይደግፋል፣

ረ) የተቋሙን የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ስትራቴጂዎችና ዕቅዶች አፈፃፀም ይከታተላል፤

ሰ) አግባብነት ያላቸው የክህሎት ሥልጠናዎች ለአካዳሚክ ሠራተኞች፣ ለተማሪዎችና ለሌሎች የተቋሙ ሠራተኞች የተሰጡ መሆኑን ይከታተላል፤

ሸ) ለምርምር፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ለዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና ለማኅበረሰብ አገልግሎት አመቺ ሁኔታና ተቋማዊ ባህል እንዲፈጠር ያደርጋል፣

ቀ) ለምርምር፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ለዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና ለማኅበረሰብ አገልግሎት የተደረገ የገንዘብ ድጋፍና ፈንዶች አስተዳደርን ይከታተላል፤

በ) የተቋሙንና የተቋሙን አባላት ከኢንዱስትሪ ወይም ከሌላ ተቋማት ጋር የሚያደርጉት የማማከር አገልግሎት ንቁ ተሳትፎ ይደግፋል፣ ይከታተላል፡፡

**፶፪. <u>በትምህርት ክፍል ደረጃ የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት አስተዳደር</u>**

፩) እያንዳንዱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚከተሉት ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡-
   ሀ) የምርምርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ኮሚቴ፣
   ለ) የአዕምሯዊ ንብረት ኮሚቴ፣
   ሐ) የምርምር ሥነ-ምግባር አጣሪ ኮሚቴ፣

፪) የትምህርት ክፍል ተባባሪ/ረዳት ዲን ወይም በተመጣጣኝ ደረጃ የተመደበ ኦፊሰር የተቋቋመው ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፡፡

፫) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኮሚቴ አባላትን ጥንቅርና ቁጥር ይወስናሉ፡፡

፬) ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እያንዳንዱ ኮሚቴ የራሱ የአሠራር ደንቦች እንዲሁም ተገልጋዮች ማመልከቻ የሚያቀርቡባቸው ቅጾች ይኖሩታል፡፡

፭) የትምህርት ክፍሎች የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና

identified and periodically updated;

c. make sure that research, technology transfer, university-industry linkage and community service activities and support systems are functional;

d. enforce the rules of this Directive regarding research, technology transfer, university-industry linkage and community service financial administration, procurement and transport services;

e. create conducive environment for technology transfer activities, and coordinate and support research that lead to the generation of technology;

f. monitor the implementation of the institution's research, technology transfer, university-industry linkage and community service strategies and plans;

g. oversee the delivery of relevant skill trainings to the academic staff, students and other employees of the institution;

h. create a conducive environment and organizational culture for research, technology transfer, university-industry linkage and community services;

i. oversee the administration of grants and funds for research, technology transfer, university-industry linkage and community service activities;

j. Support and oversee the institution's and its members' consultancy engagement with the industry or other institutions.

**52. *Research, Technology Transfer, University-Industry Linkage and Community Service Administration at the level of Academic Units***

1) Each academic unit of HEIs shall have:
   a. Research and Community Service Committee;
   b. Intellectual Property Committee;
   c. Research Ethical Clearance Committee.
2) The Associate/Vice Dean or an equivalent officer of an academic unit shall serve as the chairperson of the respective committee.
3) HEIs shall determine the composition and number of the committee members.
4) Each of the Committees referred to in Sub-Article (1) of this Article shall have their own



አዲስ አበባ

የማኅበረሰብ አገልግሎት ተባባሪ/ረዳት ዲን ወይም በተመጣጣኝ ደረጃ የተመደበ ኦፊሰር ይኖራቸዋል፡፡

፮) ውድድርንና አሳታፊነትን መሠረት ባደረገ ሥነሥርዓት፣ ተባባሪ/ረዳት ዲን ወይም ተመጣጣኝ ደረጃ ያለው ኦፊሰር በምክትል ፕሬዚደንቱ ይመደባል፡፡

፯) ተባባሪ/ረዳት ዲኑ ወይም ተመጣጣኝ ደረጃ ያለው ኦፊሰር ለአካደሚክ ዩኒቱ ዲን ወይም እንደ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ ሁኔታ አግባብነት ላለው ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪ ይሆናል፡፡

### ፶፫. <u>የፋይናንስና የግዥ አስተዳደር</u>

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቀልጣፋና ውጤታማ የፋይናንስና የግዥ አስተዳደር ሥርዓት ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ፣

ሀ) የፋይናንስና የግዥ አስተዳደር ስልጣን ባልተማከለ አሰራር በትምህርት ክፍሎች እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

ለ) የፋይናንስና ግዥ አስተዳደር ያለዕክል እንዲከናወን በተቋሙ የፋይናንስና ግዥ አስተዳደር ቡድኖች በማዕከል እና በትምህርት ክፍሎች ደረጃ ይመደባሉ፡፡

ሐ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰራተኛ ምርምር በጀት ከዓመታዊ መደበኛ በጀታቸው ቢያንስ 5% መመደብ አለባቸው፡፡

መ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለማኅበረሰብ አገልግሎት በጀት ከዓመታዊ መደበኛ በጀታቸው ቢያንስ 3% መመደብ አለባቸው፡፡

ሠ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለምርምርና ለማኅበረሰብ አገልግሎት ከያዙት በጀት ለዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና ለቴክኖሎጂ ሽግግር በጀት ይመድባሉ፡፡

ረ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለምርምር፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለማኅበረሰብ አገልግሎት የተለየ የገንዘብና የግዥ ዩኒት ያቋቁማሉ፡፡

ሰ) ተጠሪነታቸው ለምክትል ፕሬዚደንቱ የሆኑ የፋይናንስና ግዥ ሰራተኞች ይኖራሉ፡፡

ረ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የፈጠራና ኢንኩቤሽን ፈንድ በትምህርት ክፍል ደረጃ ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡

rules of procedure and standardized forms for applications by clients.

5) Academic units shall have research, technology transfer, university-industry linkage and community service Associate/Vice Dean or equivalent officer.

6) The Associate/Vice Dean or equivalent officer shall be appointed by the Vice President based on competitive and participatory procedures.

7) The Associate/Vice Dean or equivalent officer shall be accountable to the respective academic unit Dean or the respective office heads as per the context of the HEIs.

### 53. Finance and Procurement Administration

HEIs shall put in place efficient and effective financial administration and procurement system. To this effect:

a) Procurement and financial administration powers shall be adequately decentralized to academic units.

b) Project finance and procurement teams, both at the central finance administration and academic units' finance, shall be designated for the smooth running of all stages of project finance administration and procurement.

c) HEIs should allocate at least 5% of their total annual recurrent budget for staff research.

d) Community Service budget of HEIs should be at least 3% of their total annual recurrent budget.

e) HEIs shall allocate University-Industry Linkage and Technology Transfer budget from their Research and Community Service Budget.

f) HEIs shall establish separate financial and procurement units for research, technology transfer and community services.

g) HEIs shall have financial and procurement personnel to be overseen by the Vice President.

h) HEIs may establish innovation and incubation funds at the level of academic units.

## ንዑስ ክፍል 2- ሥነምግባር፣ የአሠራር ደረጃዎችና መርሆዎች

**፶፬. <u>የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት የሥነምግባርና የአሠራር ደረጃዎች፡- መርህ</u>**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥነምግባር የተመላበት አካዳሚክ አውድ በመደበኛ ተግባራቸው ውስጥ እንዲታይ በቁርጠኝነት መሥራት አለባቸው፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሠራተኞችና ተማሪዎች ተግባሮቻቸውን በከፍተኛ ታማኝነትና ሙያዊ ሥነምግባር እንዲያከናዉኑ ይጠበቃል፡፡

፫) ሠራተኞችና ተማሪዎች፣ የአገሪቱን ሕገመንግሥትና ሕጎች እንዲሁም በዓለም ተቀባይነት ያላቸውን የሣይንሳዊ ማህበረሰብ እሴቶች መሠረት ያደረጉ መርሆችን መከተል አለባቸው፡፡

**፶፭. <u>ታማኝነት</u>**

፩) በማናቸውም ሥራዎቻቸው ሂደት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሠራተኞች ታማኝ መሆን አለባቸው፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር ማኅበረሰቡን እንዲሁም ሕዝቡን የሚያሳስት፣ የመረጃ ማፋለስንና መረጃ አላግባብ የመጠቀምን ተግባር አይታገሱም፡፡

፫) በዚህ መመሪያ አንቀጽ (3) ንዑስ አንቀጽ (32) በተተረጎመው መሠረት ማኛቸውንም ዓይነት የአዕምሮ ሥራ ስርቆሽ መፈፀም የተከለከለ ነው፣ ይህም በሚቀጥለው ዝርዝር ሳይወሰን፣ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ) በምልክተ-ጥቅስ ሳይጠቀሙና ምንጩን ሳይገልፁ ቃል በቃል መገልበጥ፣ ወይም የቃላት ለውጥ በማድረግ ዐረፍተ ነገሮችን ወይም ሙሉ ፓራግራፎችን ከአንድ ወይም ከዚያ ከበለጠ/ጡ ሌላ ምንጭ/ጮች በመውሰድ ምንጮችን በግልጽ ሳያመለክቱ መጠቀም፣

ለ) የሌላን ሰው ሓሳብ፣ ሥራ፣ ወይም የምርምር መረጃ/ዴታ፣ ምንጩን ሳያመለክቱ መጠቀም፣

ሐ) የኮምፒዩተር ፋይል፣ አልጎሪዝም ወይም የኮምፒዩተር ኮድ ምንጫቸውን በግልጽ ሳያመለክቱ መጠቀም፣

መ) የሌላ ሰው ከሆነ ሥራ በሙሉ ወይም በከፊል የተወሰደን ሥራ ማቅረብ፣ ወይም

ሠ) የሌላ ሰው ከሆነ ሥራ በሙሉ ወይም በከፊል የተወሰደን ሥራ፣ በሜካኒካል፣ በዲጂታል ወይም በሌላ ዘዴ በመለወጥ ማቅረብ፡፡

፬) የምርምር ታማኝነትን በሚጥሱ አካዳሚክ ሠራተኞች ላይ እርምጃ መውሰድ ይችሉ ዘንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በውስጠ-ደንባቸው

## Section 2: Ethics, standards and Principles

***54. Ethics and Standards for Research, Technology Transfer, University-Industry Linkage and Community Service: Principle***

1) HEIs shall be committed to an ethical academic environment expressed through the core functions.
2) Staff and students of HEIs are expected to carry out their academic assignments with the highest ethical and professionalism.
3) Staff and students have to live up to the principles set in the country's Constitution and laws, and relevant universally recognized values of the scientific community.

***55. Honesty***

1) Academic Staff of HEIs must be honest in all their dispositions throughout the work processes.
2) HEIs shall not tolerate the act of abusing and misusing data that misleads the research community and the public.
3) It is prohibited to engage in any form of plagiarism as defined in Article 3, Sub-Article 32 of this Directive, which includes, but are not limited to;
   a) word-for-word copying without quotation marks and acknowledgement; or paraphrasing of sentences or whole paragraphs from one or more sources without clearly indicating their origin or source,
   b) using another person's ideas, work or research data without acknowledgement,
   c) copying computer files, algorithms or computer codes without clearly indicating their origin,
   d) submitting work which has been derived, in whole or in part, from another person's work, or
   e) submitting work which has been derived, in whole or in part, from another person's work by a process of mechanical, digital or other transformation.
4) HEIs shall make rules in their internal legislation to take actions on academic staff



አዲስ አበባ

ይህን የሚመለከቱ ደንቦችን ይደነግጋሉ፡፡

፭) በሥራ ምደባው የተመለከተውን ጊዜ ተግባራዊ ማድረግ የተመራማሪዎች ግዴታ ነው፡፡

**፶፮. <u>የሰው፣ የእንሰሳትና የተፈጥሮ አካባቢ ደህንነት</u>**

፩) ከሰው ሕይወት ጥበቃ፣ ከእንሰሳት ሕይወት፣ ከተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ፣ ከደህንነት፣ ከሴኩሪቲ፣ ከዘላቂ ልማት፣ ከሰዎች የርስ በርስ ግንኙነትና መስተጋብር፣ እንዲሁም ከኀብረተሰቡ አጠቃላይ ጥቅም ጋር ተያያዥነት ላላቸውና በዓለም ደረጃ ተቀባይነት ላገኙ የሥነምግባር ደረጃዎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ራሳቸውን ተገዥ ያደርጋሉ፡፡

፪) ሰውን በመጠቀም የሚደረግ ምርምርን በሚመለከት፣ በተለምዶ ተቀባይነት ያለውን የአደጋ መጠን አስቀድሞ በማረጋገጥ፣ በምርምሩ በሚሳተፈው ሰው ላይ ሊደርስ ለሚችለው ጉዳት ምዘና ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡

**፶፯. <u>የማይገባ ጥቅም</u>**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመራማሪዎች ሌሎች የተቋሙን አባላት፣ ተቋሙን ወይም ሕዝብን በመጉዳት፣ ለራሳቸው ወይም ለሌሎች ሰዎች የማይገባ ጥቅም ከመሻት የታቀቡ መሆን አለባቸው፡፡

**፶፰. <u>የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች ምርምር ክትትል</u>**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለድህረ-ምረቃ ተማሪዎች የምርምር ሥራ የክትትል ጥራት፣ እንዲሁም በወቅቱ ስለመጠናቀቁ ተገቢውን ትኩረት መስጠት አለባቸው፡፡

**፶፱. <u>የሥራ ቡድን</u>**

በጋራና በግል በሚከናወኑ የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎቶች የሥራ ቡድን አባላት በሙያና በአካዳሚክ ተቋማት እሴቶች መሠረት በመተባበርና በመቀራረብ ስሜት ሥራቸውን ማከናወን አለባቸው፡፡

**፷. <u>የደራሲ ግዴታ</u>**

ከአዕምሯዊ ንብረት ይፋነት ጋር በተያያዘ የምርምር ውጤቶች ለሕዝብ የሚደርሱበትን ጊዜ በሚመለከት፣ ምክንያታዊነት ያለው መዘግየት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመራማሪዎች የምርምር ውጤታቸውን በማሳተም አንባቢያን መረጃ እንዲያገኙና ከዚያም በመነሳት ግኝቶቹን እንዲያሳድጉ ማስቻል አለባቸው፡፡

**፷፩. <u>የዋናው ተመራማሪ ግዴታ</u>**

አጠቃላይ የምርምር ፕሮጀክት ሥራዎች ከመከታተል ባሻገር ዋና ተመራማሪው የገንዘብ መዳቢዎች መመሪያዎች እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

that violates research honesty.

5) Researchers shall abide to devote their time according to the work load appropriation.

**56. *Safety of the Human, Animals and the Environment***

1) HEIs shall commit themselves to the universally accepted ethical values in relation to the protection of human life, responsibility towards animal life, preservation of the environment, contribution to safety, security and sustainable development, integrity in human interactions and relations, and the association with the common good.
2) In relation to research with human participants, evaluation of risk should take a participant centered approach, with the establishment of a threshold for normally acceptable risk.

**57. *Unfair Benefit***

Researchers of HEIs should refrain from seeking unfair benefit for themselves or other persons at the expense of other members of the institution, the institution and the public.

**58. *Postgraduate Student Research Supervision***

HEIs shall give due attention to the quality of the supervision and timely completion of students' research work.

**59. *Working Team***

Working teams shall live up to the values of the professional ethos and academic organizations; express collegiality and team work in the research, technology transfer, university-industry linkage and community service that they collectively and individually work on.

**60. *Author's Obligation***

Subject to the requirements of reasonable delay in relation to intellectual property disclosure process when applicable, researchers of HEIs should publish results of research so that readers may be informed and be able to build on the reported findings.

**61. Responsibility of the Principal Investigator**

In addition to overseeing the overall research project, the Principal Investigator shall ensure that



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ★ የሪከርድና ማህደር አገልግሎት ★
አዲስ አበባ

የሚመሩባቸው የፈንዶች አስተዳደርና አወጣጥ መመሪያዎች በጥንቃቄ ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፡፡

**፷፪. ፈንድና መገልገያ መሣሪያዎች**

፩) በጀቱ እንዳይባክንና አላግባብ ለሌላ ጥቅም እንዳይውል ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሠራተኞችና ተማሪዎች ፈንዶችን እና/ወይም የመገልገያ መሣሪያዎችን ለተመደቡለት ዓላማ ብቻ የመጠቀምና የማስተዳደር ግዴታ አለባቸው፡፡

፪) ፈንዶችና የመገልገያ መሣሪያዎች በተቋሙ ወይም በፈንድ መዳቢው የአሠራር ግዴታዎች መሠረት ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፡፡

**፷፫. በጽሁፍ የተሰጠ ይሁንታና ነፃ ፈቃድ**

ከምርምር ጋር ተያያዥነት ባላቸው ተግባራት እና/ወይም በማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራት ሰዎችን የምርምር ተሳታፊ ማድረግ የሚቻለው በጽሁፍ ባረጋገጡት የምርምር ተሳታፊ ይሁንታና በነፃ ፈቃዳቸው አማካይነት ነው፡፡

**፷፬. የግላዊ ማንነት ይፋ አለመደረግ ጥበቃ**

በአገሪቱ ሕግ ተቃራኒ ግዴታ ከሌለ በቀር፣ የምርምር ተሳታፊዎች ምስጢራዊ የግል መረጃቸው ይፋ እንዳይወጣ ወይም ማንነታቸው ይፋ አለመደረጉን ለማረጋገጥ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማናቸውንም ተገቢ የጥንቃቄ ርምጃ ይወስዳሉ፤ ማናቸውም ምስጢራዊ መረጃ ወይም ግላዊ ማንነት ይፋ ሊሆን የሚችለው በምርምር ተሳታፊዎች ይሁንታና ነፃ ፈቃድ መሠረት ነው፡፡

**፷፭. የፍላጎት ግጭት**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካዳሚክ ሠራተኞችና ተማሪዎች፣ በተቋማዊ ተግባሮቻቸውና በሌሎች ማናቸውም ፍላጎቶቻቸው ወይም ግዴታዎቻቸው መካከል የፍላጎቶች ቅራኔ ከሚፈጥር ሁኔታ ውስጥ በሚያስገባ በማናቸውም ተግባር ውስጥ አይሳተፉም፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካዳሚክ ሠራተኞች፣ ማናቸውም ውጫዊ የሙያ ተግባሮቻቸው ወይም ፍላጎቶቻቸው፣ እንደመምህራንና እንደምርምር ሱፐርቫይዘሮች ለተማሪዎቻቸው ሊሰጡ የሚገባቸውን አገልግሎት የሚያጓድል/የሚጎዳ መሆን የለበትም፡፡

**፷፮. አደገኛ ማቴሪያል**

፩) በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የአደገኛ ማቴሪያሎችን አጠቃቀምና አወጋገድ የሚካሄደው

the funding agencies' guidelines as well as the guidelines on the management and disbursement of funds provided by the HEIs are followed scrupulously.

**62. Funds and Equipment**

1) HEIs' staff and students shall have an obligation to use funds and/or equipment for the purposes for which they were awarded and managed accordingly to ensure that the budget is neither wasted nor misappropriated.
2) Funds and equipment should be used in accordance with the Institution's or the awarding agency's requirements.

**63. *Written Informed Consent and Free Will***

A research participant's involvement in research-related and/or community service activities shall be through their own written informed consent and free will.

**64. *Protection of Privacy***

HEIs shall take all necessary steps to ensure privacy and confidentiality of all personal information of research participants; any divulgence of confidential information or privacy must be based on the informed consent of the research participants unless otherwise required by the laws of the country.

**65. *Conflict of Interest***

1) Academic staff and students of HEIs shall not engage in any activity that places them in a conflict of interest between their official institutional activities and any other interests or obligations.
2) As teachers and supervisors of research, academic staff of HEIs shall not allow any outside professional activities or interests to affect their responsibilities to students.

**66. Hazardous Material**

1) The use and disposal of hazardous materials in HEIs shall be subjected to the applicable laws



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

በአገሪቱ ተግባራዊ በሆኑ ሕጎች መሠረት ነው፡፡

፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አደገኛ ማቴሪያሎችን በመጋዘን የሚያቆዩበትንና የሚያስወግዱበትን ሥርዓት ይዘረጋሉ፡፡

## ንዑስ ክፍል 3- ግብዓቶች

**፷፯. <u>የቴክኖሎጂና የንግድ ሥራ ኢንኩቤሽን ማዕከላት</u>**

ቴክኖሎጂን ወደ ንግድ ሥራዎች ማሳደግ እንዲቻል፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቴክኖሎጂና የንግድ ሥራ ኢንኩቤሽን ማዕከላት ያቋቁማሉ፡፡

**፷፰. <u>የሳይንስና የቴክኖሎጂ ፓርኮች</u>**

፩) ሁኔታው የሚያስችል ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሁሉ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለምርምና ዕድገት ዓላማ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ፓርኮችን ያቋቁማሉ፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመካከላቸው ያሉትን የስምምነት ቃሎችና ሁኔታዎች የሚገዛ ውልን መሠረት በማድረግ የቴክኖሎጂ ፓርኮችን በጋራ ማቋቋምና ማስተዳደር ይችላሉ፡፡

፫) ሚኒስቴሩ ይህን የመሰሉ ፓርኮች ይቋቋሙ ዘንድ ያመቻቻል፣ ምክር ይሰጣል፣ እንዲሁም በጋራ አስተዳደር ይሳተፋል፡፡

**፷፱. <u>የመስክ ጣቢያዎች</u>**

የምርምር፣ የማኅበረሰብ አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የልማት ተግባራትን በሚመለከት፣ ሙከራዎችንና ሠርቶ-ማሳያ ለማካሄድ የሚያስችሉ የመስክ ጣቢያዎችን ለማቋቋም፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከክልልና ከአካባቢያዊ መስተዳድሮች ጋር በመሆን አስፈላጊ ዝግጅቶችን ያደርጋሉ፡፡

**፸. <u>ክላስተር ቤተ-ሙከራዎች</u>**

፩) በክላስተር የተሰባሰቡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር፣ የማስተማር፣ የምርምር፣ የኢኖቬሽን እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ጥረቶቻቸውን የሚያግዙ፣ እጅግ የዘመኑ እና አመችነታቸው ተጠብቆ የተገነቡ ቤተ-ሙከራዎችን አቋቁመው በጋራ ያካሂዳሉ፡፡

፪) ቤተ-ሙከራዎቹን በውጤታማነት ስለመጠቀምና ስለተቋማዊ አጋርነት፣ ክላስተር ቤተ-ሙከራዎች ውስጠ-ደንቦችና መመሪያዎች ይኖሯቸዋል፡፡

፫) ሚኒስቴሩ ቤተ-ሙከራዎቹ እንዲቋቋሙ ያመቻቻል፣ ይደግፋል፡፡

of the country.

2) Notwithstanding Sub article (1) of this article, HEIs shall establish a system to store and dispose hazardous materials.

## Section 3: Resources

**67. *Technology and Business Incubation Centers***

HEIs shall establish technology and business incubation centres to support the development of technologies into businesses.

**68. *Science and Technology Parks***

1) HEIs shall, whenever practicable, establish a science or technology park for research and development purposes.

2) HEIs may establish and manage technology parks jointly based on contractual agreement that governs the terms and conditions of their relationship.

3) The Ministry shall facilitate and advise the establishment of such parks and participate in its joint management.

**69. *Field Stations***

HEIs shall make necessary arrangements with regional or local governments to establish field stations to undertake experiments and demonstrations in relation to research, community service, technology transfer and development activities.

**70. *Cluster Laboratories***

1) Clustered HEIs shall establish and jointly operate state of the art, built-to-suit laboratories to assist their teaching, research, innovation and technology transfer endeavours in consultation with the Ministry.

2) Cluster laboratories shall have rules and regulations for the effective utilization of the laboratories and institutional partnership.

3) The Ministry shall facilitate and support the establishment of the laboratories.

**፸፩. የቤተ-ሙከራ ሠራተኛ**

፩) ተገቢው ችሎታና በቂ ቁጥር ያላቸው ባለሙያዎች በምርምር ቤተ-ሙከራዎቻቸው የሚሠሩ መሆኑን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያረጋግጣሉ፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በትምህርት ክፍል ደረጃ በተከታታይነት የአቅም ግንባታን ያካሂዳሉ፡፡

፫) ውጤታማና ትጉህ የቤተ-ሙከራ ባለሙያዎችን በሥራ ላይ ማቆየት ይቻል ዘንድ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቤተ-ሙከራ ባለሙያዎችን የሥራ ሁኔታ ተወዳዳሪና ሳቢ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

፬) ሚኒስቴሩ የቤተ-ሙከራ ባለሙያዎችን ጥቅማ ጥቅም በተመለከተ አሰራር ያበጃል፡፡

**፸፪. ማተሚያ ቤትና የሕትመት ማዘጋጃ**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደረጃውን የጠበቀ ቴክኖሎጂና በበቂ የሠለጠኑ ሠራተኞች ያሏቸው ማተሚያ ቤት ይኖሯቸዋል፡፡

፪) ጽሁፎች በጠንካራ የግምገማ ሂደት እንዲያልፉ ማድረግን፣ ከፍተኛ ጥራት ያለው የኤዲቶሪያል ቦርድ እንዲሁም ብቃት ያለው አርታኢ ቡድን ማቋቋምን ጨምሮ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በስመ-ጥርነት ረገድ ዓለም-አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የሕትመት ማዘጋጃ ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡

**፸፫. የትራንስፖርት አገልግሎት**

፩) የትራንስፖርት አገልግሎትና ፋሲሊቲን በሚመለከት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሚያቅዱበት ወቅት፣ ከፍተኛ ቅድሚያ ከሚሰጧቸው መካከል የምርምር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የማኅበረሰብ አገልግሎቶች ይካተታሉ፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተሽከርካሪዎችን ከዋና መንገድ ውጪ ለምርምር፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለማኅበረሰብ አገልግሎቶች ተግባራት ያሰማራሉ፡፡

፫) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተሽከርካሪዎችን ለምርምር፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለማኅበረሰብ አገልግሎቶች ተግባራት በቋሚነት ይመድባሉ፡፡

**፸፬. የቤተ-መጽሐፍትና አይ ሲ ቲ አገልግሎቶች**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቤተ-መጽሐፍታቸውን በተሟላ የሕትመትና ኦንላይን ተነባቢ ምንጮች/ ማጣቀሻዎች ለማሟላት ወቅታዊና የላቀ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ አቅማቸውን ያሳድጋሉ፡፡

፫) ለምርምር መረጃ/ዴታና ለምርምር ውጤቶች፣ እንዲሁም በፓተንት ለተጠበቁ ቴክኖሎጂዎች፣ የከፍተኛ ተቋማት የመረጃ ቋት ይኖራቸዋል፡፡

፬) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለምርምር፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለማኅበረሰብ አገልግሎቶች

**71. *Laboratory Staff***

1) HEIs shall make sure that their research laboratories are staffed with qualified and sufficient number of professionals.
2) HEIs shall provide continuous capacity building at academic unit level.
3) HEIs shall make the working conditions of laboratory professionals competitive and attractive in order to retain productive and committed laboratory professionals.
4) The Ministry shall put in place the benefit schemes for laboratory professionals.

**72. *Printing Press and Publishing House***

1) HEIs shall have their own printing press equipped with standard printing technologies and well-trained personnel.
2) HEIs may establish publishing house that meet international standards for reputability, including the requirements for rigorous review process of manuscripts, high quality editorial board, and competent in-house editorial team.

**73. *Transport Service***

1) Higher education institutions shall treat research, university-industry linkage and technology transfer, and community service transport services as one of top priorities in planning their transportation facilities.
2) HEIs shall designate off-road vehicles to research, technology transfer and community service activities.
3) HEIs shall allocate vehicles to research, technology transfer and community service activities on permanent basis.

**74. *Library and ICT Services***

1) HEIs shall give utmost attention to equip their libraries with up-to-date print and online references.
2) HEIs shall develop their ICT capacities.
3) HEIs shall establish database for research data and outputs and patented technologies.
4) HEIs shall have a sharing platform for research, technology transfer and community service among themselves.



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

አጋዥ የሆነ የመጋራት መድረክ ይኖራቸዋል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፸፭. እውቅና ያገኙ የምርምርና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለሚኒስቴሩ ስለማስገባት**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዕውቅና ያገኙ የምርምር እና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በጆርናል የታተሙ የምርምር ጽሁፎች፣ መጽሐፍትን የመጽሐፍት ምዕራፎችን፣ እንዲሁም የኮንፈረንስ ውጤት ሕትመቶችን መልክ ለሚኒስቴሩ ያስገባሉ፡፡

**፸፮. የአካዳሚክ ሠራተኞች የሥራ ስምሪት**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሙሉ ጊዜ አካዳሚክ ሠራተኞች በመምህርነት ሊቀጠሩ የሚችሉ ሲሆን፣ በዚህ መደብ የተቀጠረ ሠራተኛ የሥራ ጊዜውን 060% ለማስተማርና ተማሪዎችን ለማማከር፣ 25% ለምርምር፣ 15% ለማኅበረሰብ አገልግሎት እና/ወይም ለቴክኖሎጂ ሽግግር ያውላል፤

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሙሉ ጊዜ አካዳሚክ ሠራተኞች በምርምር ሠራተኝነት ሊቀጠሩ የሚችሉ ሲሆን፣ በዚህ መደብ የተቀጠረ ሠራተኛ የሥራ ጊዜውን 60% ለምርምር፣ 25% ለማስተማርና ተማሪዎችን ለማማከር፣ 15% ለማኅበረሰብ አገልግሎት እና/ወይም ለቴክኖሎጂ ሽግግር ያውላል፡፡

፫) በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለመምህርነት የሚያበቃ መስፈርቶችን የሚያሟሉ የምርምር ሠራተኞች፣ በተቋሙ ትምህርት ክፍል የሥራ ምድብ (ሆም ቤዝ) ይሰጣቸዋል፡፡

፬) የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች ለምርምርና ለማኅበረሰብ አገልግሎት/ለቴክኖሎጂ ሽግግር የተመደበውን ጊዜ በአግባቡ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አግባብነት ያለው የአስተዳደርና የግምገማ ሥርዓት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

፭) የሠራተኞች ግምገማ መሥፈርቶች በምርምርና በማኅበረሰብ አገልግሎት/በቴክኖሎጂ ሽግግር የተደረጉ ክንውኖችን ማካተት አለባቸው፡፡

፮) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዚህ አንቀጽ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የውስጥ ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን ያዘጋጃሉ፡፡

**፸፯. የመመሪያው ተፈጻሚነት**

፩) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የተቋማቱ አመራር፣ ሠራተኞች፣ ተማሪዎችና ሌሎች ሠራተኞች፣ እንዲሁም በሚኒስቴሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው፣

## Part Six
## Miscellaneous Provisions

**75. *Submission of Accredited Research and Technology Outputs to the Ministry***

HEIs shall submit their accredited research and technology outputs in the form of journal articles, books, book chapters and conference proceedings to the Ministry.

**76. Academic Staff Deployment**

1) A full-time academic staff of a Higher Education Institution may be employed as a teaching staff in which case he shall deploy 60% of his time on teaching and student advising, 25% on research and 15% on community services and/or technology transfer.
2) A full-time academic staff of a HEI may be employed as a research staff in which case he shall deploy 60% on research, 25% of his time on teaching and student advising and 15% on community services and/or technology transfer.
3) Research staff shall be provided with home-base by academic units as long as they fulfill the minimum criteria of teaching at the HEIs.
4) HEIs must have proper management and evaluation system to ensure that full time staff have properly implemented the allocated time for research and community services/technology transfer.
5) Staff evaluation criteria should include engagement in research, and community services/technology transfer.
6) The HEIs shall devise internal policies and guidelines for the implementation of the provisions stated in this Article of this Directive.

**77. Enforcement of the Directive**

1) HEIs, their management, staff, students and other employees as well as the responsible officers of the Ministry have the duty to respect and enforce the provisions of this Directive.



የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የማክበርና የማስፈፀም ግዴታ አለባቸው፡፡

፪) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በምርምር፣ በዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ እንዲሁም በማኅበረሰብ አገልግሎት ተግባራት ለሚሳተፉ ሠራተኞች የማትጊያ ሥርዓት ይነድፋሉ፡፡

፫) እያንዳንዱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም አካዳሚክ ሠራተኛ በምርምር፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና በማኅበረሰብ አገልግሎት በንቃት መሳተፍ አለበት፡፡

**፸፰. የውስጥ መመሪያዎችና ደንቦች**

የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርና የማኅበረሰብ አገልግሎት የሚመሩበትን የውስጥ መመሪያዎችና ደንቦች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያወጣሉ፡፡

**፸፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሂሩት ወልደማርያም (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

2) HEIs shall devise an incentive package for staff engaged in research, University-Industry Linkage and technology transfer and Community Service activities.

3) Every academic staff of higher education institution shall actively participate in Research, Technology Transfer, University-Industry Linkage and Community Service.

**78. Internal Rules and Regulations**

HEIs shall develop their own internal guidelines, rules and regulations that govern research, technology transfer and University-Industry linkage and Community Service subject to the provisions of this Directive.

**79. Entry into Force**

This Directive shall enter into force on August 2019.

Hirut Woldemariam (Professor)
Minister

Hirut W/Mariam Teketel
(Professor)
Minister